# ደጁ ጠባብ ነው

አመሰግናለሁ፣ ወንድም ነቪል። አመሰግናለሁ። ዳግም ወደ እግዚአብሄር ቤት መምጣት እንዴት ደስ ያሰኛል። የትም ሄጄ፤ ወደዚህ ድንኳን መመለሴ ሁሌም ያስደሰተኛል። ይህ ስፍራ ተመልሼ እንድመጣ የሚያደርገኝ የሆነ ነገር አለው። ኦህ፡ እንደው፡… ፓስተር የሆንኩባት የመጀመሪያና ብቸኛ ቤተክርስትያኔም ናት። እንደገና ወደዚህ መመለስ መልካም ይመስለኛል። እና በዚያች ቀን ጸሀይ ብርሃኗ ከልክላ ከዋክብትም ብርሃናቸው የሚጨልምባት ጊዜ ላይ፤ ከዚህ ጉባኤ የሆኑ በበጉ ደም የታጠቡ አንዳንዶች፤ በዚያ እንደሚገኙ አምናለሁ። ያቺ ቀን ትናፍቀኛለች።

2 ወደ አዳራሽ ስገባ፡ እህት አርጋንብራይትን እዚያ አገኘኋትና። በኪንግስተን በነበረ ጉባኤ የተካፈሉ አንዳንድ ሰዎች እዚህ እንዳሉ ነገረችኝ፤ እኔም… በዚያ ቀን ከነበሩት… ሰዎች፤ ምስክር የሚሆኑ ሰንቀበል ደስታየ ነው። እስኪ በኪንግስተን ጀማይካ ጉባኤ የነበራችሁ፤ ባላችሁበት፤ ከፈቀዳችሁ እጆች ከፍ አድርጉ። አዎ፡ እዚያ ጋ፡ እዚያ ከኋላ። በጣም ጥሩ፡ መልካም ነው።

3 የኦራልን ማስታወቂያ አይቻለሁ። ጉባኤዎቹ አስተዋውቃችኋል መሰለኝ። ቀኑን በተመለከተ፡ ትናንትና ድረስ፡ አላወቅኩም ነበር። በስድስት የሚጀምር ይመስለኛል፡ አይደል? ከስድስት እስከ አስራ አምስት፡ ወንድም ሮበርትስ በሎይስቬል። ስለዚህ፡ ሄዳችሁ ስሙት። ወንድም ሮበርትስ፡ እውነተኛ የክርስቶስ ባርያና—የቅርብ ወዳጄ ነው። እርግጠኛ ነኝ፡ በመልዕክቶቹ በየምሽቱ ትባረካላችሁ። ደግሞም… የሱ፡ እሱ ለበሽተኞች ሲጸልይ፡ እናንተም ጌታ ሲሰራ ታያላችሁ—እርግጠኛ ነኝ፤ ወንድም ሮበርትስ፡ እግዚአብሄር በኃይል የሚጠቀምበት፡ የእምነት አርበኛና ታላቅ ሰው ነው። አገልግሎቱም እያደገ ነው…

4 ወንድም ሮበርትስን ለመጀመርያ ጊዜ ስተዋወቀው ትዝ ይለኛል፡ በሚዙሪ፣ ሴንት ሎይስ፤ ተራ ዳስ ውስጥ ነበር። አይደለም፡ እኔ የነበርኩት… በካንሳስ ከተማ፡ በሚዙሪ፡ ነው። በካንሳስ፡ ካንሳስ ሲቲ፡ አዳራሽ ውስጥ ነበርኩ። ከፊት ቁጭ ብሎ ነበር። ጉባኤው ሲያልቅ፡ ወደ ጀርባ ሄደን አወራን። ከእሱ ጋር አስተዋወቁኝ። ኦራል በአርባዎቹ ክልል ላይ የሚገኝ፡ ታናሼ ነው። ስለዚህ እንዲህ አለኝ፦ “ለበሽተኞች የምጸልየው ጸሎት ጌታ የሚሰማኝ ይመስልሃል? ”

እኔም፦ “ወንድሜ፡ ሰው ሁሉ የሚጸልየው ጸሎት ይሰማል አልኩት።” እናም፡ ጀመረና፦ “ይሄው እንግዲህ! አለ፡”

5 በጣም ብልህ ሰው ነው፡ የኮሌጅ ትምህርቱም፡ የአራት አመት የሳይኮሎጂ ምሁር፡ እጅግ ብሩህ ሰው ነው—እርግጠኛ ነኝ። አሁንማ በዙርያው የአማካሪዎች ስታፍ፣ እና የመሳሰሉ ነገሮች ወደ መኖር አድጓል፡ በደንብ፡ አስላስሎ፡ እስከ መናገር ድረስ— ደርሷል። እርግጠኛ ነኝ፡ እጅግ ትባረካላችሁ።

6 ስለዚህ አሁን አጠር ያለ ምስክርነት ልሰጣችሁ ጌታ ኢየሱስ በፖርቶሪኮ እና በጃማይካ በነበረች አጠር ያለች ጉባኤ ያደረገውን ላጫውታችሁ። ብዙ

ጥሪዎች ስለሚደርሱኝ፤ እዚያ መሄዱ ተአምር ነበር። ስለ ስልክ ጥሪዎቹ፡ ሊዮ ያውቃል… በአንድ ሳምንት ውስጥ፡ በመቶዎች የሚቆጠሩ የስብሰባ ጥሪዎች ይደወላል። ልክ እንደዚህ ግን፡ ወደምሄድበት በምሪት ሲሆን ደስ ይለኛል። እንድመጣ ሰው ልኮልኝ ከሄድኩ፡ በዚያ ቤተክርስቲያን ወይም በዚያ ድርጅት ስም ነው የመጣሁት ማለት ነው። ወንድም ነቪል መሄድ አለብህ ስላለኝ ከሄድኩ፡ በወንድም ነቪል ስም እሄዳለሁ ማለት ነው። እኔ ግን ኢየሱስ ሲልከኝ መሄድ እወዳለሁ፡ ስለዚህ ህዝቡን ለማገልገል፡ በጌታ ኢየሱስ ስም መሄድም ትችላላችሁ።

7 እና ደካክሞኛ ስለ ነበር፡ አልጋየ ላይ ጋደም ብየ ነበር። ከዚህ ሽለቆ፤ ሳልውል ሳላድር፡ ሽለቆውን ለቅቄ መውጣት አለብኝ፡ ጉሮሮዬን እየጎዳኛ መቋቋም በማይቻል ደረጃ እያሳመመኝ ነው። እንዴ ሄጄ ብመለስ ይሻላል… ባለፈው፡ እኔ እና ሌዮ፡ በፍሎሪዳ ረግረግ ቦታዎች ደርሰን፡ በአርባ ማይልስ ውስጥ ተመልሰናል፤ አርባ ማይልስ በኋላ በሎይስቬል ተወኛ፤ ጉሮሮየ ፍጹም ዳነልኝ። ወንድም ባንክስ ዉድ ዛሬ ጠዋት እዚህ ሳይሆን አይቀርም። ከኪንግስተን እና ከፖርቶሪኮ ስንመለስ—በቀደምለት ጉሮሮየ ፍጹም ጽድት አለልኝ፤ ከአውሮፕላኑ ሰወርድ፡ ደህና ነበርኩ፤ ወደ ጀፈርሰንቪል ከመድረሳችን በፊት ግን፡ እንደገና ተዘጋ። እያችሁ፣ ሽለቆው ነው። እየሩ ውስጥ ያሉት ተህዋሲያን ናቸው፡ ወይም ጌታ ራሱ፡ ምናልባት፡ ሊያርቀኝ ፈልጎ ይሆናል። ስለዚህ፡ እኔ—አልገባኝም። ጸልየበታለሁ ብዙ ጊዜ ጠይቄአለሁ።

8 ብቻ፡ የሆነው ሆኖ፡ በማለዳው ሶስት ሰዓት ነበርና፡ ገና መንቃቴ ነበር። ሚስቴ እና ትንሹ ልጄ ተኛተዋል። ተነሳሁና በአልጋው ጠርዝ ላይ ሆኜ፡ በአንድ ሰፊ ቦታ ላይ ብዛት ያለው ህዝብ ተሰብስቦ አየሁ፤ ከዛ ቢሊ ፖልን "ወደዚያ ሄደህ ህዝቡን የጸሎት ካርድ ስጣቸው፡" አልኩት።

9 እሱም፦ "እሺ፡ አባቴ" አለኝ። ጥቂት ደቂቃ ቆይቶ መጣና፦ "ለዚህ ሁሉ ህዝብ የጸሎት ካርድ መስጠት አይቻልም" አለ። "እዚያ ጋር የቆመው ሰውየ ይታይሃል? " አለኝ፤

"አዎን፡" አልኩት።

10 እንዲህ አለ፦ "እዚህ ነበር፡ እኔም 'የጸሎት ካርድ የምትፈልጉ ሁላችሁ፡ እጃችሁ ከፍ አርጉ' አልኳቸው።" እና ሲናገር፦ "የጸሎት ካርድ ልሰጠው ስሄድ፤ ወደ ሌላ ቦታ ሄዷል። ወደዚያ ስሄድ ደግሞ፡ እንደገና ወደ ሌላ ቦታ ሄዷል። አሁን ደግሞ እዚያ ማዶ ጋር ሄዷል።" "አንዲት የጸሎት ካርድ እንኳን መስጠት አልቻልኩም" አለኝ።

11 እኔም አልኩት "ደህና፡ ቢሊየ፡ የጸሎት ካርድ መስጠት አይጠበቅብህም፤ ሁሉንም ሰው የሚያስተናግድ በቂ ቦታ አለን… " አየህ፡ ጸሎት ካርድ የሚያስፈልገን… ግርግር ለመከላከል ስርዓት ለማስያዝ ነው። እንዲህ አልኩት፦ "ኦህ፡ ካለን ሰፊ ቦታ ስለማይበልጡ፤ ሁሉንም እዚያ ወስጄ፡ ስልፍ አስልፌ ለእያንዳንዳቸው ልጸልይላቸው እችላለሁ።"

12 "እሺ ይሁን።" ብሎኝ፤ በስተቀኝ በኩል ዞረ እና ተለይቶኝ ሄደ። እኔም **ወደዚህ** አቅጣጫ ዞርኩኝና፤ **ወደዚያ** ሲሄድ እሱን እያየሁት ነበር።

13 ወድያውም ከሰማይ፦ “በዚህ ጊዜ ግን አንተን ከፍ ከፍ ማድረግ እጀምራለሁ፡” የሚል ድምጽ ሰማሁ። እኔም አየሁ፡ የዚህን ዓይነት የህዝብ መንጋ እየተመመ፡ ከየአቅጣጫው ሲሰበሰብ አይቼ አላውቅም።

14 ከዚያ የወንድም ሮበርትስ ስም ተጠራና፦ “አሁን ወንድም ሮበርትስ ሰላም ሊልህ ይመጣል፡” አለኝ።

እኔም፦ “ወንድም ሮበርትስን እንዴት አድርጌ ሰላም ልበለው? ” አልኩኝ።

“እሱ ሰላም በሚልህ ዓይነት” አለኝ።

15 ከዛ፡ ወንድም ሮበርትስ በጥቁር ሱፍ፡ ቢንግ ክሮዝቢ የሚለብሰው ዓይነት ትንሽ ኮፍያ ለብሶ አየሁት፤ በትንሹ ወደላይ ታጥፈው፤ ወደ ታች ገርበብ የሚሉት ጥቁር ኮፍያዎች። እኔም ትንሽ ከፍ ብየ ቆሜአለሁ፡ ወደ ላይ አየና፦ “ደህና ነህ፡ ወንድም ብራንሃም፡” አለኝ።

እኔም እጁን ጨብጬ፦ “እንደምን አለህ፡ ወንድም ሮበርትስ፡” አልኩት።

“በጣም ብዙ ህዝብ ተሰብስቦልሃል፡” አለኝ።

16 እኔም፦ “ብዙ ህዝብ እንጂ፡ ወንድም ሮበርትስ” አልኩት። እሱም ቢሊ በሄደበት መንገድ፡ ወደ ቀኝ በኩል ዞረና ሄደ።

17 ከዛ ማሰብ ጀመርኩ፦ “የቱጋር ሆኜ ነው የምሰብካቸው? ” ለመናገር አመቺ የሚሆነኝ ቦታዎች ሁሉ ሞከርኩ። እነሱን የምናገርበት አመቺ ቦታ ማየት ስላልቻልኩ—ተሰፋ እንደመቁረጥ፡ አይነት ሁኔታ ውስጥ ገባሁ።

የሆነ ሰው ግን፦ “ደህና፡ ወደዚህ ና” አለኝ።

18 እኔም፦ “ግን፡ እዚያም ቢሆን ምንም የተሻለ አይታያችሁም” አልኩት። ከዚያ ቦታውን መሻገር ጀመርኩ። ወድያውም ይህ ትዝ አለኝ፦ “በእግዚአብሄር እና በልጆቹ ፊት፡ ሁልጊዜ፡ ማድረግ ያለብኝ ዋና ነገር ትሑት መሆን ነው፡” አልኩኝ።

19 ከዛ በኋላ ከሕልሙ ወጣሁ። አሰብኩ፡ “ምን ማለት ይሆን? ወይም የት ይሆን—ቦታውስ የቱ ጋር ሊሆን ይሆን? ምናልባት በሆነ ቦታ ላይ ይህ እና ያ ይኖረናል... አያችሁ፡ አንዳንዴ፡ በራእይ ውስጥ፡ የት እንደሆነ አይነግራችሁም፡ እሱ—እንዲሁ ይናገራል እናንተም... በቃ፡ እንደ እንቆቅልሽ ነው። እናንተ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ይህ እንደምትረዱት እርግጠኛ ነኝ።

20 ከዚያ በኋላ ከፊት ወዳለው ክፍል ሄጄ ትንሽ ቁጭ አልኩ፣ እና ሊነጋጋ ሶስት-ከሰላሳ ወይም አራት ሰዓት ነበረ። ሀይለኛ እንቅልፍ እንቅልፍ አለኝ። እና ሄጄ ጋደም አልኩኝና፡ ህልም አየሁ፡ ህልሙም እጅግ ያልተለመደ ህልም ነው። ብዙዎቻችሁ ከማናጀሮቹ አንዱ፡ ጃክ ሞርገ ታውቁታላችሁ። ወንድም ጃክ ሞርገ፡ ብዙ ዓመታት እንተዋወቃለን። ከሴት ልጁ ጋር በፍቅር ቀጠሮ የወጣሁ ይመስለኛል፡ ትንሿ ጃኪ፡ የአስራ ሰባት አመት ልጃገረድ፡ ወደ አንድ ዳገት፡ እጇን ይዤ እየመራኋት አየሁ። ገና፡ ጡት የምትጠባ ጨቅላ ሳለች ጀምሮ አውቃታለሁ። አሁን ግን ልጅቷን ይዤ፡ በኮረብታው በኩል፡ ሶስት የከተማ መተላለፍያዎችን ሄድኩ። ከዚያ አንድ ትልቅ ዛፍ ጋር ደረሰንና፡ ቁጭ አለች። እና ልክ ዛሬ ብዙ ትናንሽ አፍላ-ልጃገረዶች፡ ሲለብሱት የምታውቁት፡ ዝርግት ቀሚስ፣ አይነት ቀሚስ ለብሳለች። ቀሚሱን ያዝ አደረገችና እንደመዘርጋት ነገር አድርጋው ቁጭ አለች። እና እንደ ወጣት ጓደኞች ደጋግመን እንተያያለን፣ እጆቿን **እንዲህ**

አጣምራ ሰማይ ሰማዩን ማየት ጀመረች። እንደው፡ በጣም ጥሩ ልጅ፣ እሷ ግን ሰፋፊ ትልልቅ ዓይኖች ያላት፣ ጸጉሯም አሸዋማ ዓይነት ፀጉር፣ እምብዛም የማትሰብ፡ ነገር ግን ትክክለኛ ወጣት እመቤት ናት። ሰማዩን ስትመለከት አይኗ አየሁት፡ አቤት ሰማዩ በአይኖቿ ውስጥ እንዴት እንደሚያንጸባርቅ።

21 ከዚያ፡ አምስት ፊት ያክል ከሷ ራቅ ብየ ሄድኩኝና በጎኔ **እንዲህ** ጋደም አልኩኝ፣ ሰንጥር ነገር አፌ ውስጥ ከትቼ፡ ሰንጥሩን እንዲህ አኝከዋለሁ። ማሰብ ጀመርኩ፡ "እዚህ ምን እሰራለሁ? እንዴት፡ ሽማግሌ ሆኜ፡ ከዚህች ወጣት ልጅ ጋር። ለምን፡" እንዲህ አልኩ፦ "እግብቻለሁ ብዙ ልጆች አሉኝ። ከዚህ ወጣት ሴት እዚህ ምንም ጉዳይ የለኝም።"

22 እና መነሳት ጀመርኩ። እና፡ ስነሳ፡ ከዛፉ ላይ ድምጽ መጣ፣ "ይህ ለምልክት እና ለምክንያት ነው፡" አለኝ።

23 ነቃሁና፡ ለመጮህ ትንሽ ቀረኝ፡ ቅዠት—ነው። ምን ይሆን ብየ አሰብኩ፦ "ኦህ፡ ባክ ላደርግ ይሆን ወይስ የሆነ ነገር ሊገጥመኝ ይሆን?" እሺ፡ "አይምሮየን ልጠቀም ብሞክር፡ ሁሉንም አደባልቀዋለሁ ብየ አሰብኩ፣ ስለዚህ፡ እግዚአብሄርን ብቻ ልጠብቀው።" ስለዚ መጸለይ ጀመርኩ። "ጌታ ሆይ፡ ማታ ካየሁት ራእይ ጋር የሚያዛምድ ነገር ይኖረው ይሆን፡ ምን ማለት ነው?" አልኩ፣

24 አንድ ሰዓት ያህል፡ ትንሽ ከጠበቅኩ በኋላ (ሚስቴ ተነስታ ቁርስ አዘጋጅታለች።)፣ ወድያውም ድምጹ ተመልሶ መጣና፦ "ወደ ኪንግሰተን ሂድ፡ የምታደርገው እዚያ ይነግሩሃል" አለኝ።

25 ስለዚህ፡ ወድያውኑ ወደ ኪንግሰተን ሄድኩ። እኔ እርብ እዚያ እንደምመጣ—እነሱ የሰሙት ሐሙስ ከሰዓት ነው። የሰራነው ማስታወቅያ ይሄው ብቻ ነበረ። እንዲህ ዓይነት ነገሮች ላይ... ? ... የሰው ብዛት መገመት ላይ፡ ጎበዝ አይደለሁም፡ ምክንያቱ ብዙ ጊዜ አጋንናለሁ። ብቻ በመጀመርያው ምሽት ላይ፡ አስራ ሁለት፣ ኦህ፡ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሰዎች፡ ነበሩ፡ ከታወቀ ገና አንድ ቀኑ ብቻ ነበረና። በሚቀጥለው ቀን ሯጮች፡ በጋራው ላይ፡ አራት ማይልስ መሰናክል ሩጫ ነበራቸው። አንድ ሯጭ ለአራት ሰዓታት ያህል ይሮጣል፡ ከዚያ በኋላ ሌላ ሯጭ ወደ ተራራው ይሮጣል። እና ቀጣዩ ማታ ላይ ወደ አምስት ሺ ገደማ መጡ። በሶስተኛው ምሽት ወደ አስራ አምስት ሺ ይገመታል፡ ምናልባትም ሀያ። ሺዎች ጊዜ ሺዎችም ወደ ጌታ የመጡ ነበሩ።

26 ስለዚ ራእዩ፡ ትንሿ ቤተክርሰትያን ናት፡ ልጅቷ ድንግል ነበረች፡ ህጻን ናት፣ ይህም የቤተክርሰትያኒቱ ድንግልና ማለት ነው። ጋራው ላይ የሄድኩባቸው ሶስቱ የከተማው ጎዳናዎች፡ ያገለገልኩባቸው ሶስት ቀናት ናቸው። እቺ ድንግል ቤተክርሰትያን በእኔ አገልግሎት፣ ደሴቱ በሙሉ እስክትናወጥ ድረስ፡ ከነበረችበት፡ ከፍ ወዳለ ወደ እግዚአብሄር ነገሮች አወጣኋት።

27 ኦህ፡ አገልጋዮችና፡ በዙርያ የሚኖር ህዝብ ሁሉ፡ እያለቀሱ ሲለምኑን ሲማጸኑን፣ የከተማው ሀላፊዎችም "አንድ ሁለት ቀን ብቻ፡" አሉን።

28 ከዚያ ተነስተን ወደ ፖርቶሪኮ አለፍን። እዚያም፡ ከታላቅ ድል ጋር ተገናኘን፡ ሺ ጊዜ ሺ መኪናዎች ተጨናንቀው፣ እርባ ሺ ድንቅ ነፍሳት ወደ ጌታ ኢየሱስ እንደመጡ ይገመታል። እና በመሄጃችን ላይ... እኔ አሁን የምናገረው፡ ለቤተክርትያኔ እንደሆን ተሰፋ አደርጋለሁ፡ አደባባይ ላወጣው አልችልም፡ የኛ

ባልሆኑ ሰዎች ዙርያ፡ በተሳሳተ መረዳት ሊያዩት ስለሚችሉ። የዳኛው ስም ግን ወረቀት ላይ አስፍሬዋለሁ፣ እሱና የስራ ባልደረቦቹ፡ እዚህ ጋር፡ ትተናቸው ስንወጣ የተናገሩት ነው።

29 እኔም... እሱ—ሲናገር “በዚህ ደሴት ብዙ አገልጋዮች በመምጣታቸው አክብረውናል” አለ። እንዲህ አለ፦ “አቶ/ ቢሊ ግራሃም ደሴቱን ለቆ የተመለሰው በቅርብ ነው፡” እንዲህ አለ፦ “እጅግ ድንቅ—ጉባኤ ነበረን፡” “ቢሊ ግራሃም ግን ሁሌ የምንሰማው ዓይነት ወንጌል ይዞ ነበር የመጣው፡” አለ። አለም፦ “አቶ/ ሮበርትሰም በዚህ ደሴት በመቀበላችን ክብር ተሰምቶናል፡” ሲናገር፦ “እና አቶ/ ሮበርትስ ጋር የሶስት-ቀናት ጉባኤ ነበረን። ግን፡” አለ፡ “የሆቴል ወጪዎች እጅግ ብዙ ሆነብን፡” “ሶስት ቀን ለሆቴል ወጪዎች ብቻ፡ ሰላሳ-አምስት ሺህ ዶላር ጥሎብን ሄዷል፡” አለ። እንዲህ አለ፦ “ከዚያ በኋላም ታላቁ የክርስቶስ ባርያ፡ አቶ/ ኦስቦርን መጥቶ ነበር። ግን፡” አለ፦ “አቶ/ ኦስቦርን ሲመለስ፡ ታላቅ ኪሳራ ገጠመን፡” “ያለን ሁሉ የጠፋብን እስኪመስል ሆኖ ነበር፡” አለ።

30 “ግን፡” ይላል፦ “ከዚህ ጉባኤ ያስተዋልነው ወንድም ብራንሃም እንዲጸልይለት ተብሎ ወደ መድረክ የሚወጣ ብዙም አልነበረም። ግን፡” አለ፦ “ጉባኤው ከተጠናቀቀ በኋላ፣ ከጉባኤው ብዙ ወንበሮች እና ምርኩዞች ወዘተ በመኪና ጭነን፡ ለቅመናል።” እንዲህ አለ፦ “እግዚአብሄር ወደ እኛ ወረደ እንጂ፡ በዚህ ጊዜ ሰው አልመጣም፡” አለ።

31 እኔም አልኳቸው፦ “የእኔን ጸሎት አትጠብቁ፡ እንዳችሁ በሌላው እጃችሁ ጫኑና ጸልዩ።” ደግሞም አንድ ወይም ሁለት ደርዘን ወደ መድረኩ ያመጡልኛል፣ እና፡ ልብ መነበብ ሲጀመርማ፡ ህዝብ ሁሉ ይጮኻል። ያረፍነው አራት-ኮከብ ሆቴል ውስጥ ነበር፡ ወጪዎቻችን እና ጉዞአችን እራሳችን፡ ከፍለናል።

32 እናንተ እራሳችሁ፡ በላካችሁልኝ አስራት፡ ይሄን ለማድረግ ረድታችኋል። ያ ነው የሆነው። ደግሞም ይሄን እንድታውቁ ፈልጋለሁ፡ በዚህ ሁሉ፡ እናንተ አላችሁበት። በሚመጣው ታላቅ ቀን፡ እግዚአብሄር ይሸልማችኋል። አያችሁ፡ እናንተ የሌላችሁ...

33 አንድ ሰው በራሱ ሄዶ አንዳች ነገር ቢሰራ፡ ከዚያ፡ አያችሁ፡ ሰውየው ለቆ ሲሄድ፡ የሚያስቡት፦ “ታላቅ ውርደት ነው፡ ጌታ ትቶናል ይላሉ።” ጌታ አይተዋችሁም። ሁሌ ከእናንተ ጋር ነው። አያችሁ፡ እንደ፡ እንደ ሰው ራሳችሁ ናችሁ መግባት ያለባችሁ። ጌታ ስለ ተልዕኮው ማንም ሰው ሊጠቀም ይችላል፡ ያ ማለት ግን ሰውየው በጌታ ላይ የራሱ ምርጫ አለው ማለት አይደለም። በእግዚአብሄር ዘንድ የሚኖራችሁ የራስችሁ እምነት ነው።

34 እና ደግሞ ይሄዱና በህጻናት-ተሽከርካሪ ዓይነት፡ የድሮ መንኰራኩሮች አርገው ያመጡአቸዋል፣ እና—በላያቸው ካርቶን አንጥፈው፡ ሰዎቹን በመንኰራኩሮቹ ላይ አርገው ይገባሉ። ጉባኤው ካለቀ በኋላ፡ የመሮጫው ሜዳ ባዶ ይሆናል፡ ያረጁ ጋሪዎች፣ ያረጁ ትልልቅ ወንበሮች፣ ምርኩዞች፣ ቃሬዛዎች፣ እና አልጋዎች ሁሉ በመኪና ይጫናል፣ ደግሞም የጌታ መገኘት በዚያ ስለነበረ፡ ጥለዉት ወደመጡበት ይመለሳሉ። ማየት የምንፈልገው ይህ ነው። እግዚአብሄር በስራ ላይ ስለሆነ፡ ሰዎች ከሰዕሉ ይውጡ።

35 ወዲህ ስንመለስ፡ ማለዳውን ለማበጀት፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ንግግሬን ጀምራለሁ። ወጣቶቹ ቅጂውን እንዳይለቁት ጠይቄአቸዋለሁ። "ምን እናገራለሁ?" ብየ ሶስት ቀን ሙሉ እጅግ ሳሰብ ነበር። እና ዛሬ ጠዋት፡ ከመውጣቴ በፊት፡ በልቤ ውስጥ ለቤተክርስትያን ከበድ ያለ ማስጠንቀቅያ ተሰማኝ። "ቴፑን ቅዱት፡ ነገር ግን ለሽያጭ አታቅርቡት፡" ብየ ነገርኳቸው።

36 ከመጀመራችን በፊት ግን፡ አጠር ያለች ምስክርነት ልስጣችሁ፡ የባረከኝ ምስክርነት ነው። እናንተም ተባረኩበት። ሊዮ እና ጂን ከእኔ ጋር፡ ለሶስት-ቀናት አሳ ለማጥመድ ወጣን፡ ልጄ ቢሊ ፖል እና ሚስቱም ሆነን፣ ከጆርጂያ እዚህ ጉባኤ ድረስ፡ ወደሚመጣው ጓደኞችን ሄድን። እና ውኋ ወዳለበት ቋጥኝ ወሰዱን፡ አሁን የት እንደሆነ አላውቀውም፣ ኦኪቼቢ ወይም አቅራቢያ ነው፡ ሰሚኖል ኢንዲያኖች የሚጠሩበት መጠርያ አላውቀውም። ብቻ ግን፡ ብዙ ማይሎች፡ እርቀን ነበርን።

37 እና የወንድም ኢቫንስ ወንድም፡ እንደው ኃጥያተኛ ሰው ነው። ጎበዝ አሳ አጥማጅም ነውና፡ ከጥቂት ወራት በፊት ወደነዚህ ኩሬዎች መጥቶ ያውቃል። "ግራውንድ ራትለር" የሚሏቸው እባቦች አሉበት። ግራውንድ ራትለር ነድፎት፡ ከሞት ነው የተረፈው። እግሩ አብጦ፡ ወደ ዶክተር ወሰደው መርፌ አሰወጉት። በጣም መርዛማ ናቸው። ሌላም በዚያ ቦታ ኮተንማውስ የሚሏቸው በብዛት አሉ፡ ኮተንማውሰ፣ ሞካሲን፣ ሀያ ፊት የሚያካክሉ አዞዎች አሉበት።

38 አሳ ስናጠምድም፡ ባዝ የሚሉት ትልቅ አሳ ያዝኩኝ። ኦህ፡ ደስ የሚል—የመዝናናት ቀን ነበር። እና ትልቅ ከመሆኑ የተነሳ ከውኃው እንኳን ለማስወጣት አልቻልኩም፡ ጎትቶ እራሱን ነጻ አወጣና፡ ከሜንጦው ወድያው ተላቆ ሄደ። ደግሞም ብዙ ባዞች አገኘን፡ አንዳንዱ እስከ መቶ ሐምሳ ፓውንድ የሚመዝን ባዝ። አንዳንዶቹም፡ ከአራት እስከ ሰባት፣ ሰምንት ፓውንድ ጀምሮ፣ ብዙ ፓውንዶችን ይመዝናሉ። ይሄኛው ትልቁን ያዝኩትና፡ አመለጠኝ።

39 እና እንደገና ወረወርኩ፣ እና—ሌላ ስድስት፣ ሰባት ፓውንድ ሌላ ያዝኩ። ሊሊ አበባን ከሚያቅፈው በላይ የምንደገፍበት ረዥም ግንድ ይዤ ነበር። ወንድም ኢቫንስ ደግሞ... ያቆረ ውሃ ስለሆነ፡ ውሃው ላይ ስንራመድ ሁላችንም በሰብሰናል። እና ጫማውን አውልቆ ሱሪዎችን ወደ ላይ ሰብስቦ፡ አነስ ያለች ደረቅ ቦታ ላይ ቁጭ ብሏል፡ ልብሶቹን እያደረቀ አይነት ነበር። ውሃው ላይ እየተራመድኩ ወደሱ አቅጣጫ እየሄድኩ፡ ቋጥኞቹ ጋር ትልቅ ዓሳ ሲታገል ያያል። "ቆይ ወንድም ብራንሃም፡ ቆይ አንዴ፡ እኔ እይዘዋለሁ፡" አለኝ። እየሮጠ ሄደ። አሳውን ጎተት ሳደርገው፡ የሞተ ያህል ሆኖ ነበር፡ ቅጠሎቹ ዙርያ ይንሳፈፋል። እና ሊያነሳው እየሮጠ ሄደ። እና፡ ልክ ሲደርስ፡ ዋይ አለና፤ ወደ ኋላ ተመለሰ። ራትለር እባብ ነድፎታል።

40 ሄደን ስናየው፡ እባቡ የነደፈበት ቦታ እግሩ ላይ ቀዳዳዎች ይታያሉ፤ አይኖቹ እንባ እስኪያቀሩ ድረስ እጅግ አመመው። አጥንቶቹ ሽባ የሆኑ አይነት ተሰማኝ፡ አለ። እኛም እጅግ ማይልስ ርቀን፤ በውሃው ቋጥኝ ውስጥ ነን። እንዳንሸከመው ትልቅ ሰው ነው። እና እባብ ሲነደፋችሁ፡ በጥቂት ደቂቃ ውስጥ እስከ ሞት ድረስ እጅግ ትታመማላችሁ። ሌዮም እዚያ እንዲሁ ቆሞ ነበር፡ "አንተ አሁንም አምላክ ነህ!" የሚል ነገር ልቤ ላይ ብቅ አለብኝ። እና እግሩን እንዲህ ጨምቆ ይዞት ሳለ፣ ራትለሩ በነከሰበት ሰፍራ ሁለቱ ቀዳዳዎች ላይ፣ እጆቼን በቦታው ላይ ጭኜ፡-

“ጌታ ሆይ፡ በቃልህ ላይ፣ ‘እባቡንና ጊንጡን ይረግጣሉ፤ የሚጐዳቸውም ምንም የለም’ ተብሎ ተጽፏል አልኩኝ።” በዚያች ቅጽበት፡ ህመም ሁሉ ከእግሩ ጠፋ። ጫማውን አጥልቆ ቀኑን ሙሉ አሳ ሲያጠምድ ዋለ።

41 ማታ ገብተን የሆነውን ነገር አጫወታቸው፡ እነሱም፦ “ወደ ዶክተር ብትሄድ ይሻላል” አሉት።

42 እሱም፦ “እግዚአብሄር ይሄን ያህል ጊዜ ከጠበቀኝ፡ ቀሪው መንገዴ እሱ ይጠብቀኛል” አላቸው። ሶስት ቀን አጠመድን፡ ህመም የለ ችግር የለ።

43 እግዚአብሄር አሁንም እግዚአብሄር ነው። ቃልኪዳንን ሁሉ ይጠብቃል። በአገልግሎቴ ዘመን፡ እግዚአብሄር በእባብ በተነደፈ ሰው ላይ ሲሰራ መጀምርያ ቀኔ ነው፡ ምክንያቱም በእባብ ለተነደፈ ሰው ስጸልይ ይህ የመጀመርያ አጋጣሚዬ ነው። ቃልኪዳኑን የሚጠብቅ መሆኑን እና ቃሉ ሁሉ መልካም እንደሆነ፣ ይህን ብቻ እወቁ። አሜን።

44 የዛሬ ማታ እና በሚቀጥለው ዕሮብ መርሐ ግብሮቹን አሰቧቸው። አሁን እንዲጸለይለት የሚፈልግ አንድ ሰው አለ ጸልዩለት፡ እሱም እኔው ነኝ። ደግሞም፡ ወንድም ሮበርትስ፡ ወደ ከተማው ሲመጣ ጉባኤው ለመካፈል አትርሱ፡ ከቤተክርሰትያንም ሰላምታ አቅርቡልን።

45 የእግዚአብሄር ቃል ከማንበባችን በፊት፡ ለአፍታ ያህል—በእግሮቻችን እንድንቆም እፈልጋለሁ። እስኪ፡ ያለ ሙዚቃ፡ ድንቅ የቤተክርሰትያን ጥንታዊው አዝማች አንድ ወይም ሁለት እንዘምር፣ **እምነቴ አንተኑን ያያል**። በጣም ጥሩ፤ እሰኪ ሁላችንም ከእኔ ጋር አንድላይ፡ እንዘምር። እንዴት እንደምትዘምሩ አትጨነቁ፤ ለእግዚአብሄር ክብር ብቻ ዘምሩ። ትመራናለህ፡ ወንድም ነቪለ?

እምነቴ አንተኑን ያያል፡
አንተኑን የቀራንዮው በግ፡
መለኰታዊው መድሐኒት፡
ጸሎቴን አሁን ሰማኝ፡
ኩነኔ አሁን አንሳልኝ፡
ኦህ ከዛሬ በኋላ
የአንተው ሰው አርገኝ!

በህይወት ድንግዝግዝ ሰኣዝ፡
ኀዘን በዙርያዬ ሲሰራጭ፣
አንተኑ መሪ ሁነኝ፡
ጨለማውን ገፈህ ብርሃን አርግልኝ፡
ሀዘንን ጠርገህ፡ ፍርሃትን ገፈህ፡
እንድሰት አትፍቀድ
ከጎንህ አልራቅ።

46 አንገታችንን ዝቅ እንዳደረግን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ጽሑፎች ማንበብ እፈልጋለሁ፣ ከቅዱስ ማቴዎስ፡ 7ኛው ምዕራፍ፡ 13ኛ እና 14ኛ ቁጥሮች። ጌታ በሚነበበው ላይ ሙሉ በረከት ይጨምር።

**በጠበበው ደጅ ግቡ፤** ወደ ጥፋት **የሚወሰደው፡ ደጅ ሰፊ፡ መንገዱም ትልቅ ነውና፡ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤**

## ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።

47 እንጸልይ። አምላክ ሆይ፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት እና ከመቃብር እንደገና ያስነሳኸው፣ ህያው መስዋዕት አድርገህ በዚህ ማለዳ ለእኛ የሰጠኸው፣ አንተ ለእኛ በምታስባቸው ሐሳቦች ሁሉ፤ እራሳችንን አድሰን በትሕትና ህይወታችንን ለአንተ እናስገዛለን። በሐጥያት እና በመተላለፍ፡ ሙታን እና ሐጥያተኞች ሳለን፣ የሐጥያቶቻችን ዋጋ እንዲሆን፡ በሐጥያተኛ ስጋ ምሳሌ የተፈጠረውን፡ አንዲያ ልጅህን ልከሃል፤ እንደገና ከአንተ ጋር ሕብረት እንዲኖረን፡ ንጹሑ፡ ስለሐጥያተኛው ተሰቃይቷል።

48 እናም፡ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ በዚህ ማለዳ ሐጥያተኛ በመካከላችን ቢኖር፤ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን መልእክት ወደ እያንዳንዱ ልባችን እንዳያመጣ እንቅፋት ከሚሆንብን ነገር ሁሉ፣ በትህትና፡ ጌታ ሆይ፡ ከበደሎቻችን ይቅር እንድትለን፡ እንጸልያለን። በጌታ በኢየሱስ ደም እንጻን። ማናችንም... በራሳችን፡ ተራ መሆናችንን፡ አውቀን፡ ተራ መሆናችንን እንታመናለን። አንተ ግን ቅዱስ ነህ፣ እውነትም ነህ፣ አንተ ጽድቅ ነህ፣ አንተ የእውነተኛው ምሕረት ምንጭ ነህ። እናም ዛሬ ንስሓ እንደሚገቡ ነፍሳት፡ በትሕትና ዳዴ እንላለን። ከጃማይካ እና ከፖርቶ ሪኮ፣ እንደዚህ ያሉ ታላላቅ ሥራዎችን ከሠራህበት፡ ምስክርነት እንደወጣ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ የጻድቁ መምጣት ምልክት ነውና።

49 ወንድም ኢቫንስን ከእባቡ መርዝ ምታት እንዴት እንዳዳንከው፣ ምክንያቱ አማኝ ስለሆነ ነው፣ ቃሎችህም ሁል ጊዜ እውነት ናቸው። አሁንም፡ ጌታ ሆይ፡ ጠላት እኛን ከመረዘበት ከሞት ንክሻ፡ ዛሬ ጠዋት ነጻ አውጣን። ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ የፈውስ ዘይትህ፡ መንፈሳችንን አረሰርሶ ከሐጥያተኝነት ሁሉ ያንጻን። በጠላት ሀይል የተሰበረውን የስጋ አካላችንን ህመም ሁሉ ፈውስልን። በመልኮት ህልውና ውስጥ ያሉ ሁሉ፡ የተፈወሱ ይሁኑ።

50 ጌታ ሆይ፡ በተጻፈው ቃልህ ዛሬ ተናገረን። ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም፡ አንተ ግን ትሰጣለህ። ጌታ ሆይ፡ ስለመምጣትህ እንድንዘጋጅ፡ አስጠንቅቀን። ይህን ሁሉ ስለ ስሙ በኢየሱስ ስም ለመንን። አሜን።

51 ሁሌም ትንሽ አርፋጅ ነኝ፡ አሁንም ቆይቼአለሁና። የሰንበት ትምህርትም፡ ሳያልቅ፡ አይቀርም። ምክንያት ግን አለው፡ ቤት ሰመጣ ሁሌም በቂ ጊዜ እንዳለኝ አስባለሁ። ታውቃላችሁ፡ እንደውም’ኮ፡ እጅግ ችኩል ነን። ስለዚህ፡ እግዚአብሄርን ማመን አለብን።

52 ጌታችን ዘመኑ ለነበረ ትውልድ፡ ሐይማኖተኛ ለነበረ ህዝብ እንዲህ አይነት ጠንካራ ማስተንቀቅያ ሰጥቷቸዋል። እንዲህ አለ፦ “ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ፡ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።” እነሱ፡ ሐይማኖተኞች ስላልሆኑ አደሉም። እጅግ ሐይማኖተኞች ነበሩ። በቤተክርስትያኒቱ እና በሕጎቿ እንዲሁም በሐይማኖት ተቋሞች ላይ እምነት ነበራቸው፡ (በመጠኑም ቢሆንም) በአምላክ ሰላመኑ፡ ነገር ሁሉ ጥሩ መሰላቸው። እሱ ግን ጥቂቶች እንደሚገቡ ይነግራቸው ነበር።

53 ዛሬ ጠዋትም ያ ትውልድ ከዚህ ትውልድ ጋር ማመሳሰል ከቻልኩ ብየ አስባለሁ። እያችሁ፡ በአይሁድ ዘመን ሙላት መዝጊያው ውስጥ ነበር፡

ከእነሱ በፊት ስለነበሩ የተለያዩ ሰዎች እና ስለ የተለያዩ ዘመናት የተለያየ አጨራረስ ይተርክላቸው ነበር፡ ከነሱ በፊት በነበሩ የዘመን ሙላቶች የተፈጸሙ ነገሮች ሁሉ በፊታቸው እየተደገሙ መሆናቸውን ይነግራቸው ነበር። እነሱ ግን ሊገባቸው አልቻለም። እስኪ እሱ ስለ ተናገረባቸው አንዳንድ ነገሮችን እንይ።

54 ለምሳሌ፡ እግዚአብሄር በዚያ ሰው ውስጥ፡ እንደነበረ አላመኑም። መውጣት ያቃታቸው ከባዱ ፈተና ይህ ነበር፡ ሰው ሆኖ ሳለ እንዴት እራሱን አምላክ ያደርጋል። በዘመናት ሁሉ፣ በሁሉም ጊዜያት፣ አምላክ በተደጋጋሚ በሰው ውስጥ አድሯል። አምላክ በሰው ሥጋ እንዴት እንደሚኖር ማየት አልቻሉም። ሰው የእግዚአብሔር ወኪል ነው። እግዚአብሔር በየትውልዱ፡ ሕዝቡን በሰው አንደበት ይናገራል። ሁሉጊዜም ሊጠቀምበት የሚችለው ሰው ወይም የሆነ ነገር ይመርጣል።

55 በአብርሃም፡ እንዲህ መሰናከላቸውም፡ ጠቀሰላቸው። እንዲህ በማለት፡ ነገራቸው፡- “እራሳችሁን እኛ ‘የአብራሃም ልጆች ነን፡’ አብራሃም ‘አባታችን’ ነው ካላችሁ፣ ነብዪው አብራሃም፡ ቀኔን አይቷል። በማየቱም እጅግ ሀሴት አድርጓል።” ያለ ጥርጥር ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲነግራቸው የተረጋገጠለት መሲሕ መሆኑን በመጥቀስ ነበር፣ ምክንያቱ የመሲሑ ምልክቶች ይታዩበት ስለነበር። የመሲሕ ምልክቶችም፡ በእያንዳንዱ ትውልድ ላይ፡ እንዲህ ተመሳሳይ ነበር። ነገር ግን ደግሞ፤ መሲሑ እራሱን፤ አምላክ ማድረጉ፡ አሰናከላቸዋል። ይህ ሊገባቸው አልቻለም።

56 (አባታችን የሚሉት) አብራሃም፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሲገናኝ፤ ያኔም በሰጋ ነበር፣ ምክንያቱ፡ በአብራሃም ፊት፡ የጥጃ ሰጋ በልቷል፣ የሰንዴ ዳቦ በልቷል (ወተት ጠጥቷል) ቅቤም ጭምር፣ ግን ደግሞ አምላክ ነው። አብራሃም፡ ጌታን፡ “ኤሎሂም” ብሎ ጠርቶታልና፡ እሱን አውቋል፡ ትርጉሙም ሁሉን ቻይ ያሕዌ ማለት ነው። ልብስ የለበሰ፣ ሰውነቱ ላይ አቧራ የነካው፣ ጥላ ፍለጋ፡ ከዛፍ በታች ቁጭ ብሎ፡ ምግብ የሚመገብ ወተትም የሚጠጣ ሰው። እነዚያ ቀዝቃዞች፣ ልበ-ክፋዎች፣ ራሰ ወዳድ፣ ጻድቅ ነን ባይ አይሁድ ግን የእግዚአብሄር ልጅነቱን አላመኑበትም፡ አብራሃምን ግን አባታችን አሉት። አሁንም ግን በሰጋው በኩል፡ ተመሳሳይ ነገር እየፈጸመ እንደሆነ አሳወቃቸው፡ አባታቸውን አብርሃምን ባገኘው ጊዜ፡ እግዚአብሔር በሌላ ሥጋ ያደረገውን። አብራሃም አምኗል። እነሱ ግን ማመን ተሳናቸው።

57 እያችሁ፡ አብርሃም ምርጫውን ሰላደረገ ከድንኳኑ በታች ተቀመጠ፣ ይቺ ምርጫም በዚች ዓለም በተወለደ ሰው ሁሉ ፊት ትቀርባለች። መልካም እና ክፉ ዛፍ በእያንዳንዱ ሰው ፊት ተቀምጧል። የወንድሙ ልጅ ሎጥ፡ እና እረኞቻቸው፡ ስለ መሬት መከራከር በጀመሩ ጊዜ፤ አብራሃም፡ ጻዲቅ ሰው ስለነበረ፡ እንዲህ አላቸው፡- “በእኛ መሀል ጥል አይሁን። መንገድህም ብቻ ምረጥ።” ይህ አጋጣሚ በአማኞች ሁሉ ህይወት ይመጣል። ሰለዚህ ዛሬ ጠዋት፡ በእናንተ እና በእኔ ፊት ናት።

58 ሎጥ ወደ ውድቀት እየሄደ መሆኑን አላሰበም፡ ነገሮች ቀላል ወደሚመስለው ወደ ሶደም አቅጣጫ ግን ወረደ። እኛም አቋራጭ መንገዶች የምናይባቸው ብዙ ጊዜዎች አሉ። “እገሌ-እከሌ የተባለውን ቸርች ጋር አባል እሆናለሁ፡ ከዛ በኋላ፡ እያችሁ፡ ማንም ምንም አይለኝም፣ የከታማው ትልቁ

ቸርች ነውና።" አቋራጭ መንገድ! ጥፋት ሲኖርብን፡ ብዙ ጊዜ፡ እንዲህ እናደርጋለን!

59 ክርስቶስ ከተከተላችሁ፡ በሰዎች እንደምትጠሉ፡ አትርሱ፣ እግዚአብሄርን በመምሰል በክርስቶስ ኢየሱስ የሚኖሩ ሁሉ መከራ አለባቸውና። ወደ ክርስቶስ ለመግባት፡ በየትኛውም ቤተክርስትያን ወይም የትኛውም የሐይማኖት ተቋም፣ ወይም ስርዓት አትመጡም። መግብያው በደሙ በኩል ነው፡ በቸኛው የመግቢያው ጎዳና እሱ ነው። አብሮአችሁ የሚመጣ ሌላ ሰው የለም፣ በራሳችሁ ኑዛዜ እና በግል እምነታችሁ መጥታችሁ ትቆማላችሁ። በፓስተራችሁ ወይም በእናታችሁ እምነት መሳፈር የለም። ወደ እግዚአብሄር ስትመጡ በግላችሁ ነው! አብዛኛው ጊዜ ግን የስነፍ ምርጫዎች እንመርጣለን።

60 ሎጥ፡ ሁሉንም ነገር ቀላል ሆኖ ባየ ጊዜ... ? ብዙ ገንዘብ ያለበት እና አንጋፋ የሚኮንበት ስፍራ አይቶ፣ ምክንያቱ እንግዳ ሆኖ፣ ብልጣ ብልጥ መሆን ስለሚችል፣ በሳይኮሎጂ የተሞላ፣ የተማረ ሰው ሆኖ፣ ኃይማኖቱን መከታተል ስለሚችል። እንዲህ አሰበ፦ "በእግዚአብሄር ዘንድ እምነት አለኝ፣ ወደ ሶዶም ልሂድ እና—ተጨማሪ ገቢ ልሰብሰብ፣ ከዛ በኋላ ታላቅ ሰው እሆናለሁ፣ ምናልባትም የወጣለት ሰባኪ እሆናለሁ።" አያችሁ፡ የምትመርጡት ምርጫ አለ።

61 ምእመኑ የሚመርጠው ምርጫ አለ። "እዚያ ቤተክርስትያን እሄዳለሁ። ኦህ፡ የከተማው ሰው ሁሉ አንደኛ ነው ይላል! ለምን፡ የከተማው ከንቲባ የቸርቹ አባል ስለሆነ።" አሁን፡ በጣም ጥሩ የሚባል ቤተክርስትያን አባል ሊሆን ይችላል፣ ቤተክርስትያን እና ህዝቡ ግን በቅዱስ ቃል መመዘን አለባችሁ። አንዳንዴ ወደዚህ ቦታ የሚሄዱ ሰዎች—ጥሩ ጥሩ ልብስ ይለብሳሉ በማለት፡ በአንጋፋነት ምክንያት ይሄዳሉ። እጅግ ከባድ—ስሕተት የምንሳሳተው ያኔ ነው። አሁን ይህን አስተውሉ።

62 አብራሃም፡ ማድረግ የሚችለው ብቸኛ ነገር ግን ሁለተኛው ምርጫ መምረጥ ነበር። አንዳንዴ በዚህ መልኩ ከታየ፡ ሁለተኛው ምርጫ የተሻለ ነው። አስተውሉ፡ ሎጥ ትልቋን ከተማ ለማየት፡ ጊዜ አልፈጀበትም፣ እንደው፡ ሚስቱ የጨው ዓምድ ስትሆን አልታየው፡ ከተማይቱ እሳት ሲፈጀት አልተመለከተም። አብራሃም ግን የጌታ ከሆኑት እና ከተናቁት ጥቂቶች ጋር መረጠ። በምድረበዳውም ቆየ።

63 ያውም፡ ቢሆን፡ ሳራ እንዲህ ብትለው ኖሮስ... እስኪ አስታውሱ፡ ሳራ ማለት በምድሪቱ ካሉ ሁሉ ይልቅ ውብ ናት። እንደ ሳራ ያለች ቆንጆ ሴት አልነበረችም። ያያት፡ ሰው ሁሉ፡ ያፈቅራት ነበር። አሁን ሳራ፡ ያንን ዓይነት ምርጫ ለመምረጥ እጅግ ቀላል ነበር። እሷ ግን ከአብራሃም ጋር መቆየትን መረጠች።

64 ሴቶች፡ ሆይ፡ **ከዚህ** እና **ከዚያ** ህብረት በማድረግ፣ ታዋቂ በመሆን ዲያብሎስ እያታልላችሁ። ከክርስቶስ ጋር ጽኑ! ምክንያቱ፡ ሰዓቲቱ ደርሳለች፡ ከሰዶምና ከጎመራ ይልቅ የከፋ፡ ይህችን አገር የሚያጠፋ ጥፋት፡ በደጅ ቀርቧል። ሶዶም እና ጎመራ ለምስጋና ይሆኑላታል።

65 አሁን አብራሃም፡ ከእግዚአብሄር የተሰጠውን መንገድና፣ ፍሬ የማታፈራ ምድር በተቀበለ ጊዜ፡ ባለጸጋ አልነበረም። ብቻ አንድ ነገር ያውቃል፡ የጌታ አገልጋይ እንደሆነና ጌታን እንደሚያምን።

66 ስለዚህ አንድ ቀን ሦስት ሰዎች መጡና፣ ደክመው አቧራ ለብሰው ነበር፣ አብርሃምም አዘነላቸውና፦ “ጎራ በሉና ከጥላው ስር እራሳችሁን ጥቂት እረፍት አርጉ፡” አላቸው። ንገናም ቆሞ ሲያነጋገራቸው፡ ተራ ሰዎች አለመሆናቸውን ተረዳ፣ በአነጋገራቸው። የተለዩ ነበሩ። አብራሃምም ሄዶ፡ ጥጃውን አርዶ፣ ሳራም ቂጣን ጋግራ አሰናዳችላት፡ እነሱን ለማብላት ተዘጋጀ።

67 አሁን አስታውሱ፡ ሁለቱ መላእክት ናቸው፡ የሰው ስጋ የለበሱ መላዕክት፣ አንደኛው ግን እግዚአብሄር እራሱ ነው። እና አምላክ የሆነው አንደኛው ጀርባውን ለድንኳኑ ሰጥቶ ነበር።

68 ሳራም በድንኳን ውስጥ ነበረች። እንደሷ ሰፍራዋን የምትጠብቅ፣ ባልዋ ይሄን አድርግ አታድርግ የማትል፣ ማንም የማታስጠጋ። በቤትዋ የምትቆይ ሴት ማየት እወዳለሁ። ምናልባትም ሳህኖቿን እያጣጠበች ወይም ሌላ እንደሆነ፡ ምንም አያጠራጥርም።

69 እግዚአብሄር የነበረው ይሄኛው ግን፡ ወደ ሰዶም አቅጣጫ እያየ፡ ምን ሊያደርግ እንዳሰበ አጫወታቸው። ሁለቱ መላእክት ወንጌልን ለመስበክ ወረዱ። አንደኛው ግን በዚያ ቀረ፡ እሱም አንዱ እግዚአብሄር ነበር፣ እንዲህም አለ፦ “እኔ የማውቀውን ምስጢር ከአብራሃም አልሰውረውም፡ ዓለምን ወራሽ ይሆናልና።”

70 ኦህ፡ እኛም የጌታን ምጽአት ለማወቅ፡ ቤተክርስትያ፡ ዛሬ በዚህ ማለዳ መብት አለን። ምክንያቱ፡ “ሰላም አድራጊዎች ብጹዓን ናቸው፡ የእግዚአብሄር ልጆች ይባላሉና። የሚጠሙ እና የሚራቡ ብጹዓን ናቸው፣ ይጠግባሉና። ልበ ንጹሆች ብጹዓን ናቸው፡ እግዚአብሄርን ያዩታልና። ትሁታን ብጹዓን ናቸው፣ ምድርን ይወርሳሉና።” የህያው የእግዚአብሄር ቤተክርሰትያን ምድርን የምትወርሰ ከሆነች፡ እንግዲያውስ፡ ከሷ የሚደበቅ ምስጢር አይኖርማ።

71 “አብ የነገረኝ ሁሉ፡ ነግሬአችኋለሁ፣” አለ ኢየሱስ። እነርሱ ግን አላመኑትም።

72 ስለዚህ በአብራሃም ዘመን፡ ጠቅሶ ሲያናግራቸው፡ አብራሃም መልአኩ ጋር ሲነጋገር፡ ጀርባውም ለድንኳኑ ሰጥቶ ነበር፡ አብራሃምን በልጅ እባርክሃለሁ አለው። ሳራም፡ በድንኳን ውስጥ ሆና፡ ሳቀች። እሱም፦ “ሳራ ለምን ሳቀች? አለው።” “ሳራ ለምን ሳቀች? ” ምን ለማሳየት ፈልጎ ነው? ይህ የሆነው ውድመት ከመሆኑ፡ ከጥቂት ሰዓታት ቀደም ብሎ ነበር። ከጥፋት በፊት፡ እሳት ከሰማይ ወርዶ ከተማይቱን ከመብላቱ በፊት፣ ያቺን ምልክት አደረገ።

73 ኢየሱስም፦ የሰነ መለኮት ዶክተሮችን ሁሉ፡ “ስታችኋል” አላቸው፣ ሚልዮኖች አማኞች የሞሉባት ኃይማኖታዊ አገርን። “ቅዱስ ቃል እና የእግዚአብሄር ኃይል ስለማታውቁ፡ ትስታላችሁ፡” አላቸው። እንደዚህ ላለው ትውልድ፣ በቸርች ላደጉ ሊቃውንትን፣ በደንብ ለሰለጠኑ ሰዎች። ልጅ ሲወለድ ጀምሮ፡ የቸርች ንብረት ነው። እስራኤላዊ መሆንህ የግድ ነው። አስቀድመህ እስራኤላዊ ነው፡ በተወልድክ በሰምንተኛው ቀን፡ ትገረዛለህ። የክህነት ሰርዓት ከሌዋውያን ወገን መጣ፡ በመቶዎች ዓመታት መካከል በቃል ሰልጥነዋል። ኢየሱስ ግን፦ “ቅዱስ ቃል አታውቁምና፡ ትስታላችሁ! አላቸው።” ከመማርያ መጽሐፍ እና ከኃይማኖት መመርያ ጽሑፎቻቸው ይማሩታል። ከራሳቸው ቲኦሎጂ የተማሩት ነው። ኢየሱስ ግን ሲናገር፦ “ቅዱስ ቃሉን፡

እና የእግዚአብሄር ሐይል፡ አታውቁምና። አብራሃምን ብታውቁስ ኖሮ፣ እኔን ባወቃችሁኝ ነበር። የአብራሃም ልጆችስ ብትሆኑ፡ እኔን ታውቁኝ ነበር፡ አብራሃም ቀኔን አይቶ ደስ ብሎታልና፣ በስጋ አካል ውስጥ፡ ያኔ በፊቱ በቆምኩ ጊዜ፣ እሱ ቀኔን አይቷልና። ይህን ነገር ባደረግኩ ጊዜ፡ እኔ እንደሆንኩ አውቋልና፡ ‘ኤሎሂም’ ብሎ ጠርቶኛልና። እዚህ በእናንተ ፊት ያንኑ ነገር ደግሜ ሳደርገው ግን፡ ‘ቡኤልዘቡል’ ትሉኛላችሁ።”

“ኦህ፣” “አብርሃም አባት አለን፡” ይላሉ።

“አብራሃምን ‘አባታችን’ ትላላችሁ? ”

74 እንዲህ አለ፦ “ለምን፡ እኛ’ኮ፡ የቤተክርስትያኒቱ ነን። የሐይማኖት አገር ነን። ታላቅ ህዝብ ነን። የእግዚአብሄር ህዝብ ነን!”

ኢየሱስም፦ “እናንተ’ማ ዲያብሎስ፡ እሱም አባታችሁ ነው” አላቸው።

75 ያ ትውልድ ከዚህኛው ትውልድ ጋራ ላመሳሰለውን፤ ዛሬ፡ ክርስትያን ነን የሚሉ ሚልዮኖች ሰዎች ባሉበት ዘመን፡ ሆቶንቶቶች ስለ ግብጽ ሰራዊት የሚያውቁትን ያክል እንኳን ስለ እግዚአብሄር አንዳች ነገር አያውቁም። ዛሬ ክርስቶስን እንከተላለን ክርስትያኖች ነን የሚሉ፤ ሚልዮኖች ሴቶች እና ወንዶች ቢኖሩም፣ ቀዳሚ የሆነውን መሰረታዊ የትንሳኤ ኃይሉ እንኳን አያውቁም፤ መልካምነቱን ፈጽመው አልቀመሱም። ስልጣኑን ፈጽመው ቀምሰዉት አያውቁም። ዓይኖቻቸው ለእውነት ታውረዋልና።

76 አላቸውም፦ “እውራንን የምትመሩ፡ እውራን ናችሁ። እንዲህ አይደለምን... ዕውር... ዕውርን ቢመራው፣ ሁሉም ወደ ጉድጓድ አይወድቁምን? ”

77 ደሞም፦ “ክርስትያኖች ነን። አማኞች ነን። ከቸርቾች ሁሉ በላይ በሆነው ቸርች አባል ነን። ራባዮቻችን እጅግ ምርጥ ሊቃውንት ናቸው ብለው ያስባሉ።” ኢየሱስ ግን ቅዱስ ቃሉን እንደማያውቁ ነገራቸው።

78 እግዚአብሄር ከጥበበኞች እና ከአስተዋዮች ሰውሮ፡ መማር ለሚወዱ ህጻናት እንዴት እንደሚያበራው አያችሁ? ኦህ፡ ታላቅ ኃይሉ እና ፍጻሜ-የሌለው እግዚአብሄርነቱስ! በፊቱ በፍጹም ቅንነት መሄድ ለሚፈልጉ እንዴት መልካም ነው! ከመልካም ነገር አያጎድላቸውም።

79 አሁንም በተመሳሳይ ነገር አገራችንና፣ ዓለማችን፣ የተበላሹበትን ቀን ለማየት!

80 ኢየሱስ ፈጽሞ ሊያቀናቸው ፈልጎ ነበር። እነሱ ግን፦ “ኦህ፡ አብርሃም አባታችን ነው። አትጨነቅ፡ እግዚአብሄርን ስለምናምን፡ ወደ ክብር እንገባለን። በእግዚአብሄር አምነን፡ ህዝባችንን የምናስተምር፡ ሊቃውንት ነን። አንዲት ትንሽ ምስጢራዊ ምልክት ይዘህ መጥተህ—እግዚአብሄር ይህ ነው የምትል አንተ ማን ነህ? አንተ ሌላ ሳትሆን ቢኤልዘቡል ነህ” አሉ። ይሄው፡ መመርያቸው እና የገዛ ኃይማኖት ስርዓት ነበራቸው።

ኢየሱስ፦ “ዲያብሎስ ናችሁ።” ሲላቸው አሰቡት እስኪ!

81 ያ ትውልድ ከዚህ ጋር ላመሳሰለው፡ ዛሬ ብዙ ሚልዮኖች ቸርች ይገባሉ፣ ብዙ አስር ሺዎች አሉን። እግዚአብሄርም በቤተ ክርስትያን ዳግም ለመኖር ወርዷል፣ ያኔ ያደረገው አሁንም ለመፈጸም፣ እራሱ ትላትናና፣ ዛሬ፣ ለዘላለም ድረስ ያው ለማድረግ። ሰዎች ግን አንዳንዶች እንጋፋ ለመሆን፡ ሌሎች

ምርጫን ለመሸሸ፡ በተደጋጋሚ፡ ጀርባቸውን እየሰጡት ይገኛሉ። እናንተ ግን መምረጥ አለባችሁ! ለህዝብ እንደ ግዴታ ሆኗል። "አዎን" ወይም "አይ" ማለት አለባችሁ። መኃል ሰፋሪ መሆን አይቻልም። ደጁን አልፋችሁ ስትገቡ እንደነበረ ዓይነት ሰው ሆናችሁ በፍጹም አትመለሱም። አይቻልም። ምርጫ ቀርቦላችኋል። ዛሬ ጠዋት ክርስቶስን ምረጡበት።

82 እነዚያ የቸርች አባል ሁሉ የሚድን መሰሏቸው ነበር። ኢየሱስ፦ "ደጁ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው" አላቸው።

83 ቤተክርስትያን ሆይ ዛሬ ጠዋት፡ ላስጠንቅቃችሁ፡ ተጠንቀቁ። ዛሬ በራስ-ጽድቅ፡ በራስ-መተማመን የግብዝ ትውልድ መካከል እየኖርን፡ ጊዜ ይወስዳል። ወንዶች እና ሴቶች በቤተክርስትያን ውስጥ በአግዳሚ ወንበር ሆነው፡ ለእግዚአብሄር ክብር የሚዘምሩ፣ ከቤተ ክርስትያን ወጥተው ሲጋራ የሚያጨሱ፣ ዊስኪ የሚራጩ፣ ጭፈራ ቤት የሚሄዱባት፣ እና—ለዓለም በሚኖሩባት፣ የቆሸሸ እና፣ የገማ ቀልድ እያወሩ፣ እራሳቸውን "ክርስትያን ነኝ" በሚሉበት። ወንዶች እና ሴቶች ከቤተክርስትያን ፑልፒት፣ እና የትንሳኤው ሀይል ካለበት ሰፍራ፣ የመሲሑ ምልክት በመካከላቸው ከሚሰራበት-ቦታ መጥተው፣ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት መሆን ካልተቻለ፡ የሆነ ችግር አለ። ከጥግ እስከ ጥግ፡ ጋዜጦች ሁሉ በሚያንጫጩት ጊዜ፡ ከቀዝቃዛው ሰሜናዊ ክፍለ ዓለም እስከ ደቡባዊ ሞቃት ጫካዎች ድረስ፡ እያመላለሰ፤ እግዚአብሄር ላከ፡ ሰዎች ግን ደጋግመው ጀርባቸውን ይሰጡታል። ታድያ ምን እንላለን፣ ምንስ እናደርጋለን? ወደ ተናገረበት ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መለስ ብለን እንዲህ እንላለን፦ "ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።"

84 "በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ፤ በሰው ልጅ መምጫ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል፡" ብሏል። አድምጡ፡ ኖህ በነበረበት ዘመን፡ እንደ አሁኑ ዘመን ዓለም በህዝብ ብዛት ተሞልታ ነበር። ሳይንሳቸው ከእኛ አልፎ ነበር። ዛሬ እኛ መገንባት የማንችላቸው እነ ስፊኒክስ እና ፒራሚድ ሰርቷል። [ቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] የላቀ፣ ግሩምና፣ ብልህ ህዝብ ነበር። ዛሬ ሳይንስ፦ "አንድ ደቂቃ ለእኩለ ሌሊት፡" እንደሚል አትርሱ። ሰዓቱ የሞተውን ሰዓት ከመምጣቱ አንድ ደቂቃ በፊት ሆኗል። ከምናስበው በላይ ቀርቧል። መንፈስ ቅዱስ "እንደ ኖኅ ዘመን"! ይህንን በእያንዳንዱ አማኝ ልብ ውስጥ እንደሚያስርጽ—ተስፋ አደርጋለሁ፣

85 በኖኅ ዘመን፡ ከትውልዱ ውስጥ ምን ያህል ዳኑ? ስምንት፡ ከሚሊዮኖች ውስጥ ስምንት። "በሰው ልጅ መምጫ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል፡" ብሏል።

86 "በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ፤ በሰው ልጅ መምጫ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።" ከአሰር ሺዎች መሀል፡ ሶስት ብቻ ዳኑ።

87 ምናልባትም "ሰባኪ ሆይ፡ ከእሱ ጋር ሊመጡ ያሉ ሺዎችስ ምንድናቸው? " ትሉኝ ይሆናል። አሁን፣ ወንድሜ፣ ያ በብዙ ትውልዶች የተገነባ ነው።

88 ከዚህ ትውልድ አንድ ደርዘን ቢወጣ ግን እገረማለሁ። "ደጁ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።"

89 አይይ፡ አብያተ ክርስቲያናትን የሚሉትን አውቃለሁ፦ “ስምህን በመጽሐፋ ላይ ካሰመዘገብክ እና አባል ከሆንክ፣ ትድናለህ፡ **ወዘተ**።” እንዲህ ዓይነቱ ቃል የለም። የሁሉም ስም በመጽሐፋ፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ—ከሰፈረ’ማ፡ ቢሊዮኖች ጊዜ ቢሊዮኖች እና በቢሊዮኖች ይሆናሉ፣ ሁሉንም ይገባሉ። እንግዲያውስ በየዓይነቱ መናፍስት ሁሉ ይገቡባታላ፣ ገነትስ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ትሆናለች? እስኪ አስቡት።

90 አንድ ሰውም አሁን፦ “እስኪ አንዴ ቆይ፡ ወንድም ብራንሃም። **እገሌ-እና-እከሌ፡** በልሳን ሲጸልዩ ሰምቻለሁ፡ እነሱ እንደሚድኑ አውቃለሁ።”

91 ያ ማለት በፍጹም ይድናሉ ማለት አይደለም። ጳውሎስ በመጀመሪያው ቆሮንቶስ 13 ላይ፦ “በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ፡” ብሏል።

92 “አቤት፡ **የእገሌ-እና-እከሌ** አገልግሎት ላይ ተሳተፍኩኝ። አቤት፡ የሰራው ድንቅ፡ የሰራው ታምር። ዕውርን ሲያበራ አየሁ።”

93 በዚህ ሁሉ ጭምር ሊጠፋ ይችላል። “በዚያ ቀን ብዙዎች ወደ እኔ መጥተው፡ ‘ጌታ ሆይ፡ በሰምህ አልሰበክሁምን፣ ትንቢት አልተናገርሁምን? በሰምህስ፡ አጋንንትን፡ አላወጣሁምን? በሰምህስ፡ ብዙ ተአምራት፡ አላደረግንምን? ይሉኛል’ የዚያን ጊዜም፦ ‘ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።’” “ደጁ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።”

94 የሚያሰደነግጣችሁ አንድ አሃዝ ልንገራችሁ። እንደ ህክምና ሳይንስ መሰረት፡ በቺካጎ ከተማ፡ በዶክተሮች ጥናት መሰረት፡ በሰላሳ ቀናት ውስጥ፡ ዶክተሮች በቺካጎ በያዙት ኬዝ ብቻ፡ ሰላሳ ሺ የጽንስ ውርጃ ተመዝግቧል። በውርጃ ኬዝ ብቻ፡ ምን ያህል ፒልሶች እና የመሳሰሉ ነገሮች ተወሰዷል?

95 በዩናይትድ ስቴትስ፡ እንደሚያሳየው ጥናት፣ በቅዱስ ጋብቻ ከተወለዱ ህጻናት ይልቅ፡ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱት ልጆች ይበዛሉ። መጽሐፍ ቅዱስ በዘዳግም 14:2 የሚለውን ታውቃላችሁ, አንድ “ከህጋዊ ጋብቻ ውጪ የተወለደ ልጅ፡ አራት መቶ አመታት ይወገዛል”? የልጆቻቸው የልጅ ልጅ ልጅ ልጆች ሳይቀሩ ወደ ጌታ ማሕበር መግባት አይችሉም፤ ለአራት መቶ አመታት፡ ለአሰር ትውልዶች። በአንድ ትውልድ አርባ ዓመት ሰሌት። እድመ ቅመ-ቅመ-ቅመ-ቅመ-ቅመ-ቅመ-አያታቸው ከህጋዊ ጋብቻ ውጪ የተወለደ፡ ከሰዕል ውጪ የሆነ ሰው ነበር! አሁንስ ምን? እስኪ የተቀየረበት ቦታ አሳዩኝ።

96 ወደ ምን እንመጣለን? እና በዝሙት ምክንያት፣ እና በመንገድ ላይ እንደ ወንዶች ከሚለብሱ ኃጢአተኛ ሴቶች፣ የተገኙ ህገወጥ ልጆች፣ በእግዚአብሄር ፊት ነውር በሆነ ነገር፣ ክርስትያን-ነን ከሚሉ፡ ሲጋራ አጫሾች፣ ኮክቴል ጠጪ አማኞች። እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን የጋለሞታ ሰብሰብ ይከልክልልን! አዎን። ደግሞም ራሳቸውን ክርስትያንን ብለው ይጠራሉ? ኢየሱስ፦ “ደጁ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡” ማለቱ አይገርምም።

97 እራሳቸውን ዝቅ አያደርጉም። ጠማሞች ናቸው። አስተውሉ፣ ዳዊት ስለሠራው ኃጢአት ሲነገረው፣ በፍጥነት ተጸጸተ፣ ስለዚህም እግዚአብሔር ወደደው። እነዚህ ሐጥያቶቻቸው ብትነግሯቸው፦ “ከአሁን በኋላ ፍጹም

ፊት አልሰጠውም፡” ይላሉ። ለምን? የሚሄዱባቸው ብዙ ቦታዎች አሏቸው፣ እንዲህ ዓይነቱን መቀበል ወደሚችሉባቸው ወደ ሕገ ወጥ ጫካዎች መሄድ ስለሚችሉ። ሰባኪዎች ሙሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ለብሰው ቃሉን፣ ወንጌሉን ሳያመቻምቹ የሚሰብኩበት ጊዜ አሁን ነው። ወንዶች ራሳቸውን ዝቅ ማድረግ አለባቸው።

98 ከእንግዲህ ወዲህ በክርስቲያኖች መካከል ቅንነት የለም። “እኔ ሜቶዲስት ነኝ፣ እኔ ባፕቲስት ነኝ፣ እኔ የጴንጤቆስጤ ነኝ፡” ማለት ይፈልጋሉ፣ **ይሄ** ለእግዚአብሄር ትርጉም አልባ ነው። [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ—አርታዒ።]

99 “በልሳን ተናገርኩ፣ ተአምራትን አደረግሁ።” ዓይን አሳዋሪ ከሚባሉ ነገሮች ዋና ሆኖ ሳለ፡ አትኩሮታችን ሁሉ በእዚያ ላይ እናደርጋለን። አዎን። ዝናብ በጻድቁም በሐጥያተኛውም እኩል ይዘንባል። በሰብሉ ላይ የሚዘንበው ዝናብ በአረሙ ላይም ይዘንባል፡ ሮይ። ያው ዝናብ፡ ያው መንፈስ ቅዱስ ሰዎች ላይ ይወርዳል። ያ ማለት ግን… ተፈጥሮአቸው፡ ከውስጥ ወደ ውጭ ይቀየራል ማለት አይደለም። ውጫዊ መገለጫ ወይም ማሳያ ሳይሆን፡ ውስጣዊው የሕያው እግዚአብሔር መንፈስ ነው ይህም ሰውየውን አዲስ ፍጥረት ያደርገዋል፡ በእግዚአብሄር ፊት ልቡ ወይም ልቧ ትሁት ያደርጋል።

100 እንዲህ ብትሉ፦ “ሰባኪ፡ ከዚህ ሁሉ ሚልዮን እና በዓለም ካለ አራት ቢልየን ህዝብ ደርዘንም መውጣቱ ያጠራጥረኛል ነው የምትለኝ? ” አረ የሚነጠቁ ደርዘንም ይሙሉም አይሙሉ ያጠራጥረኛል። እስቲ አስቡት! ኢየሱስ በወንጌል ውስጥ ያለውን’ኮ ነው የምነግራችሁ። አስቡት እስቲ!

101 እስቲ ምንድነው? የሥነ ምግባር ብልሹነት በሰዎች መካከል ሰለ አለ፣ ሕጋዊ ያልሆኑ ሕፃናት መወለድ ጀመሩ፣ ያም ያጠፋቸዋል። አያችሁ፡ እነዚህን የመሳሰሉ ነገሮች እየዘረዘርን ብዙ ሰዓታት መቆየት ይቻላል፣ በዚህም እኛ ያለንበት ዘመን ፈራሽ፣ ጠፊ፣ በህዝቡ-ትውልድ-መሀል-የበሰበሰ ዘመን መሆኑ ማየት ትችላላችሁ። ምንም ዓይነት ምልክት ማየት አለመቻላቸው፡ ወንጌሉን መስማት አለመቻላቸው አይደንቅም፣ ሐይማኖተኞች እና የተሰጡ ሲሆኑ፡ ደንዳኖች ናቸው።

102 ኢየሱስ እንዲህ አላለምን፦ “መንፈስ ግን በግልጥ፡ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች”? አያችሁ? አይይ፡ አዎን፡ መጮህ ትችላለህ። አዎን፡በልሳኖች ትናገራለህ። አዎን፡ እምነትህ አጋንንትን ያወጣል። እኛ የምንናገረው ግን ያ አይደለም።

103 “ወንድም ብራንሃም፣ የክርስቲያን ምልክት ምንድነው? ማን ይድናል? ትሉኝ ይሆናል፤ አንተስ፡ ወንድም ብራንሃም? ” እኔ አላውቅም። እግዚአብሄርን ብቻ እታመናለሁ። እኔ እንደሚሆንልኝ አምናለሁ። ሕይወቴን፣ በየቀኑ፣ ከቃሉ ጋር አስተያየዋለሁ። ከዚህ ቃል ጋር ካልተሰማማ፣ የሆነ ስህተት አለ፣ ስለዚ ተመልሼ ማስተካከል ይኖርብኛል።

104 “ደህና፡” “ወንድም ብራንሃም፣ ሰዎች በልሳኖች ሲናገሩ፣ ድነዋል ማለት አይደለም? ካላችሁኝ፡” አይደለም፡ ጌታዬ! በፍጹም፡ አይደለም! ጠንቋዮች

እና መተተኞች ሳይቀር በልሳኖች፣ ኩታራ ነገሮች ሲናገሩ ሰምቻለሁ። በልሳኖች የሚናገሩ ከሌላ ሰው ሚስት ጋር የሚኖሩ ሰዎች አይቻለሁ። ሰዎች በልሳኖች ሲናገሩ፣ ቤቱ በእሳት የሚነድ እስኪመስል ድረስ ወደላይ-ወደ-ታች ዘልለው ሲጮሁ አይቻለሁ፣ ከዛ በኋላ ወጥተው ክፉ ሰምምነት ሲዋዋሉ፣ ሲሰርቁ፣ ውሸት ሲናገሩ፣ ወዘተ አይቻለሁ። እንዴት ትጠብቃላችሁ? አይደለም፡ ጌታዩ።

105 የተቻላቸውን ያህል መንፈሳውያን፣ የቸርች ዲያቆናት፣ የቤተክርስትያን ናቸው። ለምን፡ እሁድ ቤንዚን የገዙ ይመስሉአችኋል አይደል? አይደለም። ሰኞ ላይ እጅግ-የወረደ ቆሻሻ ስራ ይሰራሉ። እግዚአብሄር በውጭ ሳይሆን በልብ ውስጥ ይኖራል፡ ከልብ የሚመነጭ ነገር ነው።

106 "ደጁ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።" በኖህ ዘመን እንደሆነ፣ ከሚልዮኖች ሰምንት ብቻ፤ በሶዶም ዘመን እንደነበረ፣ ከሚልዮኖች ሶስት ብቻ፤ በሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል።

107 እና ያለንበትን ጥፋት ተመልከቱት። የእያንዳንዱ ሰው፡ በሚያስበው፡ ዲያብሎስ ከዚያች የተለዩ ሰባኪ አርጎ ይሰራቸውና ፑልፒት ላይ ይወጣሉ ሰዎችም በዚያው ይወሰዳሉ።

108 ባለፈው ቀን አንድ ሰው፡- "እኔ ሴቶቼን እንዲያብዱ ስለምታደርጉብኝ፡ መድረኬ ላይ አላወጣችሁም" አለ። አይ፡ ያው ናቸው እንጂ። ወደ አእምሯቸው ይመልሳቸዋል፣ እነዚያን ልብሶች እና ወዘተ እንዲተው ንገሯቸው። ወይም፡ ደግሞ፡ አንድ ሰው ማድረግ አለበት።

109 ሚስቴን እንዲህ አልኳት፡- "እኔ እራሴ፡ እብጃለሁ እንዴ? እብድ ነኝ ወይ? ወይስ፡ እኔ ምንድነው የሆንኩት? " በኔ ውስጥ አንዳች እረፍት ያሳጣኝ ነገር አለ። ማንም ምንም ይበለኝ ግድ አይለኝም፡ መናገር አለብኝ።

110 "አገልግሎትህን ታበላሻለህ፡" በሉኝ። እሺ፣ ወንጌል የሚያበላሸው ማንኛውም አገልግሎት መበላሸት አለበት።

ጌታ ይህ ሐጥያት ነው፡ ይህም ነውር ነው እንድንል! ስለ እውነት እንድንጸና እና ስለ'ሱ እውነት እንድንናገርለት ድፍረትን ሰጥቶናል!

111 "ደጁ ጠባብ ነው፡" አለ ኢየሱስ፡- "መንገዱም የቀጠነ ነው።" እና ሚልዮኖች ሁሉ፡ ሜተዲስቶች፣ ባፕቲስቶች፣ ፕሪስቢተርያኖች፣ ጴንጤቆስጣሎች ሁሉ ይገባሉ ብላችሁ የምታስቡ፡ በዚያ ቀን ላይ ተላላ ትሆናላችሁ። ኢየሱስ ሲናገር፡- "ብዙዎች ወደ መንግስት መጥተው፡- 'እዚህ የመግባት መብት አለኝ' ይላሉ አለ።'' አለ፡- "የመንግስት ልጆች ግን ያስወጧቸዋል። በዚያም ማልቀስ እና ማንባት እና የጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" ክርስትያኖች ሆይ፡ ዛሬ ማለዳ ሂሳብ ብታወራርዱ ይሻላችኋል፣ በህይወታቸው ውስጥ ታማኝ የሆኑ፡ ክርስቲያን ነን የሚሉ አሥር እጥፍ ሚሊዮኖች ጊዜ ቢልየኖች ሰዎች፣ ደጁን አያገኙትም። ኢየሱስም ተናግሯልና።

"ስንቶች ይገባሉ? "

112 ስንት እንደሚገቡ እኔ አላውቅም። ብቻ አንድ ነገር፡- "እግዚአብሄር ከእነሱ አንዱ ያርገኝ!" ይሄው ነው። ፈራጅ እሱ ነው። "ብቻ አንዱ ልሁን።"

113 "ታዲያ ወንድም ብራንሃም አንድ ክርስትያን እንዴት ይታወቃል? " ካላችሁኝ፡

114 እኔ አላውቅም። ቅዱስ ቃል የሚለውን ግን ልንገራችሁ። በርግጠኝነት የምታምኑት ነው። መንፈስ ቅዱስ ወደ ምድር በተላከ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ተናገረ። መልአኩን ላከ—እስቀድሞ፡ ላከ። እርሱም እንዲህ አለው፦ “በከተማውና በሕዝቡ መካከል ሂድና፡ በግምባራቸው ላይ ምልክትን አድርግባቸው፡ ንስሓ የሚገቡትን እና፡ እርኩሰቱን አይተው የሚያዝኑትን እና የሚያለቅሱትን ሁሉ።”

115 እርኩሰት ምንድነው? የወንድን ልብስ የምትለብስ ሴት። እግዚአብሄር ይጸየፈዋል። አንድ አጸያፊ ነገር ባለበት አካባቢ ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? እንዴት ነው የሚያሳምማችሁ! ልትቋቋሙት አይቻላችሁም። ሴት ወንድ የሚለብሰውን ልብስ ስትለብስ፤ እግዚአብሔር የሚሰማው በዚህ መንገድ ነው፤ በመዘምራን ዘማሪ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ በየቀኑ የሚጸልይ ትሆናላችሁ፡ እና በየቀኑ የሚጮህ፡ ወይም በየቀኑ ለእግዚአብሔር የሚኖር፣ በእግዚአብሄር መገኘት ፊት ግን ትወገዛላችሁ። ቃል የሚናገረው ይህንኑ ነው። “እርኩሰት!” እና እንዲህ ከመሳሰለ ጋር የሚያብሩ እጣቸው ከዚያ ጋር ይሆናል።

116 እግዚአብሔር እንዲህ ያሉትን ለመቃወም ጸጋን ይስጠን። በራስህ መቆም ካላብህ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በእጅህ ያዝና ጽና። መቼም አይወድቅም እሱ።

117 አሁን በዚህ ጊዜ፡ ህዝቡ ወደረከሰበት፡ መልአኩም ዳግም ማሕተም እያደረገ፤ ወደሚያልፍበት ቀን ደርሰናል። ማን እንደሚድን ማወቅ ከፈለጋችሁ፡ እስኪ ከጀፈርሰንቪል አንድ ሰው ጥሩልኝ፣ በከተማችን ውስጥ የሚያዝን እና የሚያለቅስ አንድ ሰው ጥቀሱልኝ፣ በከተማዋ ስለሚሰራ እርኩሰት እየጸለየ፡ ሳያቋርጥ የሚያዝን እና የሚተክዝ። እስኪ እጃችሁን እውጥታችሁ አንድ ሰው መጥቀስ ትችላላችሁ? እንግዲያውስ ይህን ቃል ተቀበሉ፦ “ወደ ሕይወት የሚወስደው፡ ደጅ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነው፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ይሆናሉ።” የሚታተሙት እነዚህ ብቻ ናቸው።

118 አይይ፣ ወደ ቤተክርስቲያን የሚሄዱ’ማ ብዙዎች ላሳያችሁ እችላለሁ። በመዘምራን የሚዘምሩ ብዙዎች ማሳየት እችላለሁ። ብዙ የሰንበት አስተማሪዎች ላሳያችሁ እችላለሁ። የታላቁ ማሕበርሰብ መሪዎች ተብየዎች—ላሳያችሁ እችላለሁ። በልሳን የሚናገሩ ብዙዎች፣ ብዙዎች ጯሂዎች፣ ብዙ የወንጌል ሰራተኞች ላሳያችሁ እችላለሁ።

119 ግን በዓለም ባሉ ኃጢአቶች ከልቡ ያዘነ አንድ ሰው አሳዩኝ! ዛሬ ቆሞ እነዚያን ቤተ እምነቶች የሚያወግዝ ሰባኪ አሳዩኝ። ቆሞ ነገሩን የሚናገር፡ እና እነዚያን ቤተ እምነቶችን የሚያወግዝ ሰባኪ አሳዩኝ። ወድያው ያባርሩታል፣ አፉን ቢይዝ ይመርጣል፣ ሚል ቲኬቱ ነዋ።

120 ቢሊ ግራሃም ጃክ ሙርን፣ ሰብሰባዎቼ እንዴት እንደሚቆሙ አትይ፣ ማለቱ አይገርምም፣ “ባፕቲስት አይደለም፣ ጴንጤቆስጤም ሜተዲስትም አይደለም፡” ይሉኛልና። “ሁሉም ይቃወሙኛል፡” ብሏል። በርግጥ፡ ይሄ እኔ ያልኩት አይደለም… ይሄን የምልበት ምክንያት፡ መቼም በህዝብ ፊት አላወራውም። ለቤተ ክርስያኔ ግን እለዋለሁ። የፈተና ሰዓት በእኔ ላይ ስለሆነ፣ ትግል አለብኝ።

121 “ብትመጣ፡ መልካም ነው፡ በዚህ እና በዚያ ርዕስ ጉዳይ ግን እንዳትናገር፡” ይላሉ። ታዲያ እንዳፍታ መተንፈስ ብታቆም አይሻልም።

122 እግዚአብሄር ሰበክ ያለኝን እሰብካለሁ! አዎን። ከሰምንቱ አንዱ የሆነ ቦታ ላይ ይገኝ ይሆናል። አንደኛውም ሌላ ቦታ። በዚያች ቀን ግን በአንዳንድ የኃይማኖት መመርያ ወይም በአንዳንድ የቤተክርስቲያን አስተምህሮ ወይም ተቋም ማመቻመቾ ምክንያት፣ ጥፋተኛ መባል አልፈልግም። እውነቱን ሰብኬአለሁ!

123 እንዲህ ይሉኛል፦ “ወንድም ብራንሃም፡ እጅግ ድንቅ የሚመሰለው፡ አገልግሎትህ፡ እንዴት ነው፣ እንደሌሎቹ ሰዎች አገልግሎት መሰፋት ያልቻለው ለምንድነው? ”

124 ይሄው ነው። እውነቱ ይሄ ነው። እስኪ ወደ ከተማ ብገባ፣ አሰምብሊስ ኦፍ ጋድ የሚተባብሩኝ ይመስላችኋል? እኔ የማምነው አያምኑበትም፡ አይተባበሩኝም። ከሰንት አንዴ ሞናልባት አንድ። ሜተዲስቶችስ የሚተባበሩ ይመስሏቿል? አንድ ሳምንት ማናጀሬ ሁኑና። ሞክራችሁ፡ እወቁት። ከገባችሁም፡ በጌታ ኢየሱስ ሰም ትገባላችሁ። አዎን።

125 አይይ፡ እርግጥ ነው፡ አዎን፡ ይቀበሏችኋል፡ የሆነ ቦታ ላይ ይቀበሏችኋል፡ በምንም ነገር ከእነሱ ጋር የሚያገናኛችሁ አንዳንድ ነገር እንዳይኖር ነው። ከዛ በኋላ ለቃችሁ ስትሄዱ፡ እንዲህ ይላሉ፦ “አይ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ታውቃላችሁ፡ አሁንማ እእምሮው ትንሽ ለቀቅ እያለ ነው። እሱ’ኮ… ”

126 አእምሮየ ከሳተ፣ መጽሐፍ ቅዱሰም አስተምህሮው ላይ ሰተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገር ያ ነው! አዎን፡ ጌቶች። ንቁ!

127 ኢየሱስ “ለምን ‘ቡኤልዘቡል’ ትሉኛላችሁ? አላቸው፡ የሰሎሞንን ታምኑታላችሁ፡ ልብ የማንበብ ምልክቱ። የሱ ዘመን ታምኑታላችሁ። ያንን ሰጦታ ለማየት፡ የደቡብ ንግስት ክምድር ጫፍ መጥታለችና፣ አይታም አምናበታለችና። እናንተ ግን ዘወትር በፊታችሁ እያያችሁት፡ አላመናችሁትም።”

128 የገዛ ወንድሞቹም አላመኑበትም። “ወደ በዓሉ እናንተ ሂዱ፡” አላቸው፣ “እኔ ግን አሁን አልሄድም፡” አላቸው። የገዛ ወንድሞቹ ሰላላመኑበት፡ በሌላ መንገድ ሄደ። አዎን። “ደጁ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።”

129 ደቀ መዛሙርቱስ፡ የቁርጧን ሰዓት በደረሰች ጊዜ፡ የት ነበሩ? በመሰቀሉ አጠገብ አንድ ሴት እና አንድ ወንድ ነበሩ፡ ዮሃንስ እና ማርያም ብቻ። ሌሎቹ ሁሉ ሸሹ።

130 ይሄው የቁርጥ ጊዜ። ጌታ አንድ-አንድ ነገሮች የሚያደርግበት። ጊዜው አሁን ነው። መሲሕ በምድር ላይ የሚገኝበት ጊዜ ይህ ነው። የእግዚአብሄር ኃይል በህዝቡ ላይ የሚሰራበት ጊዜ ይህ ነው። እነሱ ግን ኦህ፦ “ቅዱስ-ተንከባላዮች፣ ቀውስ፣ እብዶች፡” ወዘተ፡ ይሏቸዋል። ሰዓቲቱ ግን ይህች ናት!

131 በእውነት በፍርድ ቀን ታላቅ የሆነ ሐዘን ይኖራል።

132 አይይ፡ ህገወጥ ነጋዴ፡ በፍርድ ቀን ሰፍራውን ያውቀዋል። ጠማቂም እንዲሁ መጨረሻውን ያውቀዋል። ጋለሞታም መቆምያዋን ታውቃለች። ቁማርተኛም የት እንደሚቆም ያውቃል። ጠጪውም መጨረሻውን ያውቃል። ሰለዚህ አያዝንም።

133 ታዲያ ኃዘን ማን ጋር ትሆናለች፣ ትክክል ነን ሲሉ በነበሩት ዘንድ ናት። ሀዘን የሚሆነው እነዚህ ጋር ነው። “ወደዚያ ሲቀርቡ፦ ‘አዎን፡ በስምህ አጋንንት አውጥተናል፡ ይላሉ። ሰባኪዎች ነን። ከዚህና-ከዚያ ቤተክርስትያን ነን። ታላላቅ ታምራት አድርገናል። አቤት፡ እንደጉድ ሰብከነዋል! እንዴት፡ በቤተክርስትያኒቱ ውስጥ መጋቢ—ነበርኩ። ቢሾፕ ነበርኩ። **እንዲህ** ነበርኩ።’ እናንተ ዓመፀኞች፣ ከእኔ ራቁ፣ በጭራሽ አላውቃችሁም።” ይሄው ነው። ያ ነው ብስጭቱ። እንዲህ አለ፦ “የልጅ ልጆቻቸው ወደ መንግስት ገብተው፡ ‘እዚህ የመሆን መብት አለን ይላሉ፡’ እነሱ ግን ልቅሶና ዋይታ ጥርስ ማፋጨትም ወዳለበት፡ ወደ ውጭ ጨለማ ይጣላሉ።” “ወደ ህይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።”

134 ህዝቤ ለሆናችሁ፡ ለእናንተ ለተወደዳችሁ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ይሄን ሰሙ። ቅድመ ዝግጅት አላደረግኩበትም። እኔ ለምለው ተጠያቂ ነኝ። ተጠያቂነቴ ለነዚያ ብቻ ነው። ከአሁን በኋላ በህይወቴ ሌላ ሰብከት ፈጽሜ ባልሰብክ፡ እውነቱ ይህ ነው፡ የሚድኑ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። ይሄን አስታውሱት፡ እጅግ ጥቂት ሰዎች። እናንተም ከእነሱ አንዱ ያርጋችሁ።

135 “እነማን ናቸው፡ ወንድም ብራንሃም? ” እኔ አላውቅም። የሚያውቅ ሰው የለም። በመንቀጥቀጥ እና በፍርኃት የየራሳችን መዳን እንፈጽማለን።

136 አንተ ግን ከእግዚአብሔር ጎን ተሰለፍ። የልብ ምትህ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ካልመታ፡ እንግዲያውስ የሆነ ችግር አለ፡ የሆነ ችግር አለ። ቸርቻችሁ ምንም ብትል፣ በዚያ ውስጥ አለመኳዝ። እግዚአብሔር በተናገረው ነገር መኳዝ አለባችሁ። የምትፈረዱበት መጽሐፍ፡ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከእሱ ጋር ሁኑ!

137 “ኦህ፡” “እሺ፡ እኔ’ኮ በጌታ ኢየሱስ ስም ተጠምቄአለሁ፡” ትላላችሁ። ትክክል ነው፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። ግን ህይወትህ ካልተከተለው፡ መጠመቅህ ለምንም አይበጅህም።

138 “እሺ፡ እኔ’ኮ መንፈስ ቅዱስ ተቀብያለሁ፡” ትላለህ። ጥሩ ነው፡ ማድረግ የነበረብህ ነገር ነው። ነገር ግን በውስጡ ህይወት ከሌለበትስ!

139 በሰንዴው ላይ ወርዶ የሚያበቅለውን ያንኑ ኃይል፡ አረም እንደሚያበቅል፡ አረሙንም፡ እንደሚያሳድግ፡ አስታውስ። ትንሿ አረም ልክ እንደ ሰንዴዋ ቆማ ትደሰታለች። በዚያው ህይወት ትኖራለች፡ ይህ እውነት ነው። ሐጥያተኛውም በእግዚአብሄር ህልውና ሆኖ፡ እንደ ክርስትያን፡ ድል እያወጀ ሊኖር ይችላል። በልቡ ውስጥ አንዳች የተለየ ነገር ከሌለው ግን! ክፉ መናፍስት የሚገሰጽበት ተመሳሳይ ሰልጣን’ኮ ሊኖረው ይችላል። ኢየሱስም ብሏል። ሰባኪ እንደሚሰብከው ዓይነት ወንጌልን በደንብ ሊሰብክ ይችላል። ኢየሱስ ያለውም፡ ይህንኑ ነው። መጽሐፍም እንዲሁ ያስተምራል። አዎን፡ ጋሼ። “በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፣ ሥጋዬን ለመሥዋዕት ለመቃጠል ብሰጥ፣ ድሆችን ለመመገብ ያለኝን ሁሉ ብሰጥ፣ ተራሮችን ለማፍለስ—እምነት ቢኖረኝ፣ ይህ ሁሉ ባደርግ፣ በሰሙ ብሰብክ፣ በሰሙ ዲያብሎሰን ባወጣ፣” “ከንቱ ነኝ፡” ብሏል። እና፡ ይሄን ማድረግ እየቻለ፡ ግን “ከንቱ።” ሐሳቡን አገኛችሁት?

140 አሁን፡ ማድረግ የሚገባችሁ፡ ከልባችሁ፡ ክርስትያኖች መሆን ነው፡ ከዚያ በጠባቧ ደጅ ግቡ። ወደ ጥፋት የሚወስደው መንገድ ሰፊ ነውና፣ ከአማኞች

ትውልድ መካከል ሚሊዮን ጊዜ ሚሊዮኖች በዚያ ይሄዳሉ። ምክንያቱ፡ እናንተ እና ክርስቶስ ብቻ የምትሄዱበት፡ ጠባብ ደጅ እና ቀጭን መንገድ ስለሆነ።

141 “ወደ ህይወት የሚወስደው መንገድ ቀጭን ነው፡ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።” አሁን፡ ይህ የጌታችን ቃል ነው። ማይ! ምን እያደረገ ነበር ይሆን? ቆም ይልና፡ የልብ ሐሳባቸው ይመረምራል።

142 እንዲህ አለ፡ “ቡኤልዘቡል ነው እንጂ። ይህ እንዴት አምላክ ይሆናል? እሱ ሰው ነው! ይህ ጥበብስ ከወዴት አገኘው”? አሉ በገዛ ከተማው።

143 እኔ ይህን የምለው እናንተን ሰዎች ንቄ አይደለም… ወደዚች ከተማ ስንገባ ግን፡ እንዲህ ይመስላል፣ እናንተ ክርስትያኖች ናችሁ፡ ትወዱኛላችሁ። ወደዚህች ከተማ ስትገቡ፡ ሰይጣን መትቶ የዘረራቸው ትመስላላችሁ። ይህ ቦታም ተኰንኗል። ይህች ከተማ ተኰንናለች።

144 ቢሊ ግራሃም ወደ ሎይስቪል ሲገባ ምን አለ? በህይወት ዘመኔ ካየኋቸው ቦታዎች ሁሉ ይልቅ “አጋንንት-የሞላበት ቦታ ነው” አለ። በጋዜጣ ላይ፦ “የዲያብሎስን ጫና በግልጽ የሚታይበት፡” ብለው አስፍረውታል።

145 እኔም እንዲሰማኝ፡ ግድ ነው። ለምን? ይህ ቤቴ ስለሆነ። ኢየሱስ ወደ ራሱ ከተማ በተመለሰ ጊዜ፡ ባለማመናቸው ምክንያት፡ ብዙ ተአምራት አላደረገም ይለናል። እንዲህ አለ፦ “ነቢይ፡ ወይም ሰባኪ፡ በገዛ—በገዛ አገሩ፣ በገዛ ሕዝቡ መካከል በቀር ሳይከበር አይቀርም።” አያችሁ? ቃሉም ይላልና፡ ምንም ልታደርጉት አይቻላችሁም። አያችሁ?

146 አሁን እዚህ ከተማ ውስጥ ስትራመዱ! ምንም አላውቅም እንዳትሉኝ። ስንቀሳቀስ እጄን ይጨብጡኛል ሰዎች “ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም፣ እወድሃለሁ፡” ይላሉ። ውሸት እንደሆነ ታውቁታላችሁ! ውሸት እንደሆነ ይታወቃል። እግዚአብሔር የልብን ምስጢር መናገር ከቻለ፡ እንዴት እኔን አይነግረኝም?

147 አዎን፡ በከተማው ዙርያ በህዝባችሁ መካከል! ልክ ሲያዩአችሁ፡ “አዎን፡ አንተ ታውቀዋለህ፡ እዚያ ጋር እንዲህ እና-እንዲህ… አይቼ”

“የት? የት ነው እሱ? ”

“እዚያ ላይ… ”

“እይ! እሱን ሰውየ’ማ እናውቀዋለን!”

148 ይታውቃችኋል። ልንገራችሁ፡ ብዙም የማይወዳችሁ ሰው ወደ ቤታችሁ ስታስገቡት፣ ቤታችሁ ውስጥ ትንሽ ደቂቃ ቁጭ ሲል እንግዳ የሆነ ስሜት ይሰማችኋል። እና ይሄንን በአስራ አራት ሺህ አባዙት፡ እና የምላችሁን ነገር ይገባችኋል። ከዛ በኋላ ደግሞ ሰው ሁሉ እናንተን በሚወድበት ቦታ ሂዱ፤ ያንን እንግዳ ተቀባይ ስሜት፡ ኦህ፡ ማይ፡ በቃ፡ ዘለአለም ኑሩበት ይላቿል፡ አያችሁ። ይሄ ነው፡ አያችሁ፡ መንፈስ ነው። ሰዎች ግን ምን እንደሆነም አያውቁትም፡ ብቻ የሰዎቹ መበረዝ ይገርማቸዋል።

149 መልካሞች ሴቶች፡ መልካም ሴቶች ስነ ምግባር የጎደለው አለባበስ ለብሰው እንዲወጡ የሚያደርጋቸው ነገር ምንድነው? አሁን ቅዝቃዜ እያለ እኳን ሳይቀር፤ ምንድነው፡ ገና የአስራ-ሰድት-ዓመት ሴት፡ በእናቷ ፊት መልበስ የሌለባትን ልብስ ለብሳ፤ ጎዳና ላይ መውጣት አለባት? ችግሩ፡

ልጅቷ አይደለችም (ልጅቷ ምኑንም አታውቀውም)፡ ነገር ግን ሰባኪዎች የፑልፒት ስራቸው ስለዘነጉ ነው። ይህ በእውነት ልክ ነው። እርግጠኛ ነኝ። ሴቶች የፍትወት-ልብሶች እና የመሳሰለ ነገር ለብሰው፡ ጎዳና ላይ ይወጣሉ፣ ሐጥያተኞችም ያዩአቸዋል እሷ ግን ከሰውየው ጋራ የተኛች ያህል ጥፋተኛ መሆኗን እንኳ አታውቀውም። ኢየሱስ ብሏልና! ኢየሱስ አለ፦ "ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም፣ ያን ጊዜ በልቡ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሯል፡ በፍርድ ቀንም መልስ ይሰጥበታል።" ደጁ ጠባብ፡ መንገዱም ቀጭን ነው!

150 ከባድ ሰው ብላችሁ እንደምታስቡኝ አውቃለሁ። ከባድ አይደለሁም! ወንድማችሁ ነኝ፡ ደግሞም እወዳችኋለሁ።

151 ሊመጣ ካለው ቁጣ ሽሹ! ልባችሁ በመንፈሱ እስኪሞላው ድረስ ወደ መስቀሉ ሂዱ እና አልቅሱ፣ ያ ከዓለም ነገር ሁሉ ይመልሳችኋል፣ ልባችሁ ለእሱ እየነደደም በፊቱ እግዚአብሔርን በመምሰል ትመላለሳላችሁ። ፍቅር ነው! ሽክም አይደለም። ክርስቶስ ሽክም አይደለም፡ ክርስቶስን ማገልገል፡ ክርስቶስን የሚያገለግል ፍቅር ነው። እያንዳንዱ የሕይወታችሁ ደም ስር ከእርሱ ጋር እስኪመታ ድረስ ያስጨንቃችኋል፣ ያስገድዳችኋል። ያኔ ኃጢአትን ታዩታላችሁ።

152 በምድር ላይ አለቀሰ። በኖህ ዘመን ልቦቻቸው ባየ ጊዜ፡ እግዚአብሄርን አዘነ። ኢየሱስም በተራራው ላይ ቆሞ፡ "ኢየሩሳሌም፣ ኢየሩሳሌም፣ ብዙ ጊዜ አቀፍኩሽ፡ አሁን ግን ቤቶችሽ ወና የሚሆኑባት ሰዓት ደረሰችብሽ።"

153 የእግዚአብሔር ልጅ በሚመጣበት ጊዜም እንዲሁ ይሆናል፣ የእውነተኛ አማኝ ልብ ተሰብሯል። እሱ የሚያየው ምድሪቱን የሚያጥለቀልቅ መነቃቃት መኖር አለበት ነው። በሕገ-ወጥ ሰብሰብ እንዴት ሊሆን ይችላል? ሲጀመርም የተኰነኑ ናቸው፤ እንዴት ይሆናል?

154 የእግዚአብሔር መንግሥት መረቡን በባሕር ውስጥ እንደጣለ ሰው ትመስላለች፣ ባወጣውም ጊዜ ኤሊዎች፣ ተርቦች፣ እባቦች፣ እንቁራሪቶች፣ አንዳንድ ዓሦች ነበሩበት። ማን ወደ ዳር መጣል እንዳለበት፡ መወሰን የሚገባው እሱ ነው። ወንጌልም እንዲሁ ያደርጋል። ቢሊ ግራሃም፣ ኦራል ሮበርትስ፣ እኔም፣ ሌሎች የወንጌል ሰባኪዎች ሁሉ፡ እንዲሁ ይጥላሉ፣ ወደ ውስጥ ይሰቡትና፡ "ይሄው እነዚህ፡ ጌታ ሆይ።" ዘወትር የምናደርገው ግን ምንድነው? ዳግም ከመመለሳችሁ በፊት፡ እንደገና በኩሬው ውስጥ ገብተው፡ ይገኛሉ። ምንድን ነው? ከጅምሩ ኤሊ ነው። በወንጌል መረብ መያዙ፡ አይጠቅመውም። ሲጀመር ኤሊ ነው። ሲጀመር እንቁራሪት ነው። ሲጀመር እባብ ነበር። ወደ ቤተክርስቲያን ከመግባቱ በፊት ግብዝ ነው። መጠጡን እና ቁማርን፣ ማጨስን እና ውሸትን፣ መስረቅን እንኳን ለመተው ፍላጎት አልነበረውም። ገሃነም ሰለ ፈራ ብቻ ነው የመጣው። እንዲህ ስትፈሩት እራሳችሁን የበለጠ የእሱ እጩ ታደርጋላችሁ። ያ እውነት ነው። "ደጁ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነውና፣ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።"

እንጸልይ።

155 ጌታ፡ ሆይ፡ መርምረኝ ፡ጌታየ። ጌታ ሆይ፤ የእኔን ጉዳይ አሁን መርምረው። እንዲህ ከሰበክሁ በኋላ፡ በፊትህ በፍርድ ፊት እንድመጣ አታርገኝ። ኦህ፡ አንዳች ያልነጻ ነገር በእኔ ዘንድ ቢገኝ፡ ጌታ ሆይ፡ እባክህ፡ ውሰድልኝ!

የምንኖርበት ቀን ላይ ሴቶች እና ወንዶች ሁሉ ሲደነድኑ እያየነው ነው። ተዋርደዋል። "በጽዮን ሴት ልጆች መካከል እፍረት የለም፡" ብለህ ያኔ ተናግረሃል። ከንግዲህ ወዲህ ህፍረት እስከማይሰማቸው ድረስ ጨዋነታቸው ተወሰዶአል። ጌታ ሆይ፡ እስኪ አሰቡት! አሁን ደግሞ ሰዓት ቆጣሪው እየቆጠረ እንደሆነ እወቁ፡ ከአንድ ወይም ሁለት ደቂቃዎች በኋላ፡ ታላቁ ጥፋት ይመጣል፤ ከዚያ በኋላ ርኩሱ ይርከሰ።

156 አምላክ ሆይ፣ ዛሬ ጠዋት ሁላችንንም ቀሰቅሰን። ወዝውዘን፣ ጌታ ሆይ! ምልክቶች ሲታይ ተመልክተናል። ይሄን ለማወቅ ዓይኖቻችንን ከፍተናል። ጌታ ሆይ፡ ሚልዮኖች፣ እና ሚልዮኖች፡ ጀርባቸውን አዙረው ሲሄዱ አይተናል። ጌታ ሆይ፡ ምን ላድርግ፡ ምን ላድርግ ብየ እሰባለሁ? ጌታ ሆይ፡ አንዳች ነገር ይኖር ይሆን? ጌታ ሆይ፡ መልዕክቱን ወደ ህዝቡ ለማድረስ፡ ብዙ ጸሎት፣ ብዙ ስብከት፣ ወይም ሌላ ነገር የሚጠይቀኝ ከሆነም፡ እርዳኝ። እኔ ምን ላድርግ? እነሱ እንደሆነ ዘወትር ይረሱታል። ታላላቅ ተአምራቶችህን አደረግህ ድንቆችም ፈጸምህ፣ ሆኖም ሕዝቡ አልተመለሰም። ቃልህ እንዲፈጸም ይሆን፣ ይህ ጊዜ "አባቴ ካልሳበው በቀር ማንም ወደ እኔ ሊመጣ አይችልም፡ አብ የሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል ያልክበት ይሆን"? ጌታ አምላክ ሆይ፡ ሰዎች ነቅተው የምድር መጨረሻው ምልክት ማየት ይችሉ ዘንድ አድርጋቸው። ለህዝቡ አንዳች ነገር ትሰጣቸው ዘንድ፡ ጌታ ሆይ፡ እጸልያለሁ።

157 ዛሬ ጠዋት በዚህ ያለውን ታናሽ ህዝብ ባርክልን። አምላክ ሆይ፡ ከወንድም ነቪለ ጀምር፡ ጌታየ። ዛሬ ጠዋት፡ ሆድ ቁርጠት አሞታል፡ ጌታሆይ። አካሉን ፈውሰው። የፈውስ እጅህ በእርሱ ላይ እንዲሆን እጸልያለሁ። ነፍሱንም ይዳሰሰ።

158 እግዚአብሔር ሆይ፣ በጉባኤው መካከል እለፍ። ምናልባት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ዳግመኛ ላያቸው የማልችላቸው ወንዶችና ሴቶች እዚህ አሉ፣ ያኔም ምስክሬን እሰጥባቸዋለሁና። ቃልህ ግን ሳነበው፦ "ደጁ ጠባብ ነው፣ መንገዱም የቀጠነ ነው፡ ጥቂቶች ብቻ የሚያገኙት ነው።" ጌታ ሆይ፡ አንዳንዶቹ "ከጥቂቶቹ፡" አድርጋቸው፡ ታደርጋቸዋለህ ጌታየ? እዚህ ላለ ሰው ሁሉ ይህን አድርግላቸው።

159 መጸለይ ብቻ እንደሚቻለኝ ሰው እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ በማገዝ ቢሆን፡ ይህ ህዝብ ለእኔ የማያደርግልኝ ነገር የለም። ቢርበኝ፡ ያበሉኛል። ሱፍ ቢያስፈልገኝ፡ ይገዙልኛል። ወንጌልን እንዳሰፋ፡ አንድ ላይ ሄደው መኪና ይገዙልኛል። በዚህ ጉዳይ'ማ የትኛውም ነገር ያደርጋሉ። አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ነፍሳቸውን፡ እባክህ መርምራት፡ በፊትህም ይፈትሿት ዘንድ እርዳቸው። እኔ አላውቅም፡ እያንዳንዳቸው ግን ከምርጦቹ መካከል እንደሆኑ አምናለሁ። ጌታ ሆይ፡ እኔን ጭምር፡ አሰገባኝ። ወደዚያ የማያደርሰ አንዳች ነገር ቢኖርብኝ፡ ጌታ ሆይ፡ እባክህ ግለጥልኝ፣ አሁኑኑ እታረማለሁ። ጌታ ሆይ፣ በዚያ ማለዳ በወንዙ ዳር ችግር እንደማይኖርብኝ፡ እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ። በዚያች ቀን መሄድ እሻለሁ። ዛሬም ልትሆን ትችላለች፡ ቀኒቱ መቼ እንደምትሆን እኔ አላውቅም። ሰለዚህ፣ እንዳውቅ እርዳኝ፣ እነዚህ ሰዎችም እንዲያውቁ እርዳቸው።

160 ልባችን ግድ የለሽ መሆኑን ስንረዳም! ኦህ፡ በሬድዮም ቢሆን ቸርች በመሄድ፡ ጥሩ መልዕክቶችን እናዳምጣለን። መልካም መልዕክቶችን እንወዳለን። ኢየሱስ የትም ሆኖ ቢናገር ግድ የለንም። ግን፡ ጌታ ሆይ፡ በሐዘን እና በእንባ፡ ጸንተን እየተቃወምን፡ ሁሉንም ነገር እያደረግን፣ በከተማይቱ የሚደረግ እርኩሰት፡ አይናችን እንባ እያለቀሰ፣ እና ሐጥያት ሸክም ሆኖብን ይሆን? ጌታ ሆይ፣ የእግዚአብሔር መልአክ እኛን አይቶ ምልክት ያድርግልን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

161 እንዲሁም፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን ና እና ልባችንን አዘጋጅልን፡ ከእኛ ጋር ስለመኖርህም እውነተኛውን ምልክትህ፣ ከዚህ ትውልድ መጨረሻ በፊት የፍጻሜውን ምልክት መቀበላችንን—በመቀብል ላይ መሆናችንን እንድናውቅ ስጠን።

162 በምድሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ከሌላ ሰው ሚስቶች፡ ሕገ ወጥ ልጆች እየወለዱ ሰናይ፤ እና—በየ ዓመቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሴት ልጆች እና ታዳጊ-አፍላዎች ትምህርታቸውን አቋርጠው ጎዳና ላይ እናቶች እየሆኑ፣ ክብር አይታወቅ፣ ሴቶች እራሳቸው እንኳን፡ እጅግ እየተበላሹ፡ በሲጋራ እና—በመጠጥ፣ የልጆችን አእምሮ እጅግ በሚያናውዝ በቴሌቪዥን እና በሌሎች ነገሮች መርዛማ ሆኖአል። ጌታ ሆይ፡ አንተ፡ ቅዱስ አምላክ ስትሆን! እስከመቼስ ይቆያል?

163 አባት ሆይ፡ ዛሬ—ቶሎ አንዳች ነገር መደረግ እንዳለበት፡ የሆነ ስሜት እየተሰማኝ ነው ጌታ ሆይ። ምን ማለት እንዳለብኝ አላውቅም፣ ጌታ ሆይ፣ ማድረግ ያለብን ነገር በልባችን ውስጥ እንድታኖር ግን፡ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ እነዚህን ነገሮች ስጠን። በኢየሱስ ስም ጠየቅን። አሜን።

164 ሰዓቱ ቀርቧል። ምክንያታዊ የሆነ አስተዋይ ሰው ሁሉ፣ የሆነ ነገር እንዲሆን በዝግጅት እንዳለ ያውቃል። በዚህ ህንጻ ውስጥ፡ ትክክለኛ አእምሮ ኖሮት፣ ይህች ዓለም በዚህ ሁኔታ እንደማትቀጥል የማያውቅ ሰው ሊኖር አይችልም።

ወዳጆች፡ ይሄን መቋቋም አንችልም። እኔ እንደው ዛሬ ማለዳ፤ እንደ ፓስተራችሁ እና እንደ ወንድማችሁ፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሌላ እንድትከተሉት የምመራችሁ አንዳች ነገር የለኝም። ሌላ የማውቀው ነገር የለኝም። ንጥቀት ከመፈጸሙ በፊት እንዲሆኑ በትንቢት የተነገሩትን ነገሮች አስቧቸው፣ እለ ብየ የማውቃቸው ሁሉ ተፈጽመዋል።

165 እናንተም “የአውሬው ምልክትስ? ” በሉ። በታላቁ መከራ ጊዜ የሚመጣ ነው። ያኔ’ማ ቤተክርስትያን ሄዳለች። በነዚህ ላይ ምልክት አይደረግባቸውም፡ ጨርሳ ትሄዳለች፡ አያችሁ። ምልክት ማድረግ’ማ አሁን እየተካሄደ ነው። ምልክት መደረጉ፤ መለዮው እየቀጠለ ነው። ወደ ጌታ ሽሹ፣ በፍጥነት ወደ’ሱ ሽሹ!

166 ጥቂት ደቂቃዎች እዚህ ስንቆይ፤ ግርም እያለኝ ነው ዛሬ ጠዋት። ደግሞ ያደረጋችሁት ያህል ተሰማኝ። እያንዳንዳችሁ “አምላክ ሆይ፡ መርምረኝ!” ስትሉት፡ ስሜታችሁን—እያነበብኩት ነው። የእኔም ስሜት፡ እንዲሁ ነው። ወዳጆች ሆይ፡ ይህ መልእክት፡ በህዝቡ ዘንድ ጎልቶ የሚወጣ እንዳልሆነ አስተውያለሁ። ብትገስጿቸው ደጋግሞችሁም... እንደው—ዝቅ ብታደርጓቸው። አንድ ሰው ይህን ስራ መስራት አለበት። ይህን የሚያደርግ ሌላ

ሰው በሆነ ብየም እመኛለሁ። ነገር ግን ይህን ለማድረግ ዕጣው በእኔ ላይ ከወደቀ፡ የጽዳት ሴት እንኳን መሆን ካለብኝ፡ ላጽዳ። ዳዊት ሲናገር... እኔ አለ፦ “ከሐጥያት ጋር በድንኳኖች ከመኖር፡ በእግዚአብሄር ቤት የእግር መጥረግያ ብሆን ይሻለኛል ብሏል።” ትክክል ነው። እግዚአብሄር ሁኑ ያላችሁ ነገር ሁሉ፡ አድርጉት። አትፈሩ። እንዲህ ከሆነም...

167 አስታውሱ፡ ይህ ማለት፡ ታላቅ ነገር ነው። “ወንድም ብራንሃም ስምንት ነፍስ ብቻ ይድናሉ ነው ያልከው? ” በሉኝ።

168 ስንት እንደሚድኑ እኔ አላውቅም፡ ልነግራችሁም አልችልም። አንድ ነገር ግን እላለሁ፤ እንዲህ ካለ ዘመን፡ እጅግ ጥቂት ናቸው። አስቡት እስቲ፡ እሱ በነበረበት ዘመን፡ ስንቶች ዳኑ። የኖህን ዘመን፣ የሎጥ—የሎጥ ዘመንም የሌሎቹም ሁሉ ዘመን፡ አስቡት። እንዲህ አለ፦ “የሰው ልጅ በሚመጣበት ዘመንም እንዲሁ ይሆናል፡ ምክንያቱ፡ ደጁ የጠበበ፡ መንገዱም የቀጠነ ነውና።” አየህ፡ ከእሱ ጋር፡ ብቻህን ትሄዳለህ፡ አከተመ። አየህ? “የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።” የወንጌል እውነታ እንደሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ? ኢየሱስ ክርስቶስ “የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፡” ብሏል። እጅግ ጥቂቶች ናቸው። እናንተም ከነሱ አንድ ሁኑ። ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ፣ አስቸጋሪ ነው። ስለ እናንተ ባለኝ ሰዋዊ የፍቅር ስሜት፡ ይሄን ስናገራችሁ እቸገራለሁ፡ የእግዚአብሄር ፍቅር ግን እንድነግራችሁ ያስገድደኛል።

169 እንግዲህ በአብርሃም ዘመን የሠራው ይኸው መንፈስ ቅዱስ፣ በክርስቶስ ዘመን ደገመው፣ ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ እዚህ እንደሚመጣ ቃል ገባ። ይሄው አለ። አሁን፣ እውነቱን ከነገርኩህ፣ እግዚአብሔር ለዚያ እውነት ግዴታ አለበት።

170 እኔ ቃሌን ካልጠበቅሁ፡ የቃሌ ሰው አይደለሁም። እናንተም ቃላችሁን ካልጠበቃችሁ፡ የቃላችሁ ሰዎች አይደላችሁም። ምናልባት፡ ቃል ገብቼላችሁ ላልፈጽመው እችላለሁ፡ ግን—መጥቼ ግን እነግራችኋለሁ። የእናንተ ዕዳ ኖሮብኝ፡ ከእናንተ የምደበቅ ከሆንኩኝ፡ ግብዝ ነኝ። መጥቼ ግን እንዲህ ካልኳችሁ “ዕዳህ አለብኝ፡ መክፈል ግን አልቻልኩም፡ የተቻለኝ ግን አደርጋለሁ፡” ይቅር ትለኛለህ ታግዘኛለህ። አያችሁ?

171 ሁላችንም የእግዚአብሄር ዕዳ አለብን። ሐቀኞች እንሁን። የሕይወታችን ዕዳ አለብን። ሄደን እናውራ... እንዲህ አትበሉ፦“አየህ፡ መልካም፡ እኔ አሁን—እኔ ፕረስቢተርያን ነኝ። ሜተዲስት ነኝ። ጴንጤ ነኝ። እኔ ቸርች ኦፍ ጋድ ነኝ። እኔ ናዝሪን ነኝ። ፒሊግሪም ሆሊነስ ነኝ አትበሉ።” እንዲህ አታስቡ! ከነዚህ መካከል ብዙዎች ገሃነም ይገባሉ። በክርስቶስ ሆናችሁ፡ ክርስትያን ሁኑ።

172 እስኪ አሁን ስንቶቻችሁ ናችሁ፦ “ውንድም ብራንሃም፡ በጸሎትህ አስበኝ፡ አሁን እነሳለሁ የምትሉት”? ጌታ ይባርካችሁ።

173 ጌታ ሆይ፣ እጆቻቸውን ታያለህ። ጊዜው ደርሷል፣ ታላቁ መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ጠዋት ይህንን ሕንፃ አረጋግቶታል። መገኘትህ ይታወቀኛል። ለቃልህ ክብር ብለህ እንደመጣህ አስተውያለሁ፣ “ማንም ከእኔ እጅ እንዳያወጣው፡ እኔ እግዚአብሄር ተክያለሁና፡ ቀን እና ማታ አጠጣዋለሁ።” ስራህን ለመስራት ቃልህን ልከሃልና፡ ጌታ ሆይ፡ ይህ ደግሞ—ይፈጽመዋል። ቅዱሳት መጻሕፍትም ስለ አንተ ትናንትናና፣ ዛሬ፣ ለዘላለም ያው ነህ ይላሉ።

174 በዚያ ዘመን የነበሩ ሰዎች ማመን አልቻሉም፡ መንፈስ ቅዱስ በአንተ ውስጥ እንደነበረ ማመን አልቻሉም። አንተም አምላክ ስትሆን (ሰው ሆነህ) ተገኘህ፣ ያውም፡ ከሐጥያቶች ሁሉ ሊያድነን ወደ ምድር የመጣህ በድንግል-የተወልደህ የእግዚአብሄር ልጅ ነህ። የእግዚአብሄር መንፈስ በአንተ ዘንድ በማየታቸው፡ የተለየ ነገር ለማድረግ ሞከሩ። ጌታ ሆይ፡ አንተ ግን አልካቸው፦ "በእኔ ውስጥ የሚኖረው አብ ነው እንጂ፡ ስራዎችን የሚያደርግ እኔ አይደለሁም። እርሱ ሥራዎቹን ይሠራል። አብርሃምን 'አባታችን ነው' ካላችሁት። አብራሃም ቀኔን አይቶአል።" አዎን፡ አይቷል፡ ያኔ አጠገቡ ቆሞ ሳለ፡ እነዚያን ስራዎች እና ምልክቶችን ሲያደርግ አይቶታል። "ቀኔን አይቶ ደስ አለው አልካቸው።" አላቸው፦ "መጽሐፍትን ወይም የጌታን ኃይል፣ ባለማወቃችሁ፣ እግዚአብሔር ድንግልን እንዴት እንዳጸለለላት፣ (በድንግልና ልደት) ወንድ ልጅ እንደወለደች፡ በተወለደው ሰው ውስጥም በሐይሉ ሙላት ማደሩ ባለማወቃችሁ ትስታላችሁ።"

175 መሰዋዕት እርጎ ከሰጠን ያንን አካል ይሄው ያንኑ ደም ወሰደ፣ ይኖርባቸው ዘንድ የመደባቸውን ሰዎች ይቀድሰበታል፡ እስከ ፍጻሜ ዘመን ድረስም ስራውን ይቀጥላል! አምላክ ሆይ፡ ሰዎች ይሄን ያዩት ዘንድ አንቃቸው። ሰጠን። እጃቸውን ያነሱት ሁሉ አድን። ልባቸውን አጽዳ። ጌታ ሆይ፡ እጆቼን አነስቻለሁ። አቤቱ ጌታ ሆይ፡ አንጻኝ። ይህ የመታረም ቤት ነው። ይህ ሰፍራ የምንታጠብበት ቦታ ነው። ዛሬ ጠዋት መንፈስ ቅዱስ ይጠበን፣ ከእድፈትም ያንጻን።

176 ጌታ ሆይ፡ በመንፈስህ ሳይሞላ ከዚህ የሚሄድ አንድ ሰው እንዳይኖር፡ ጸሎታችን ነው። ምናልባት ይህ ሲሆን ከበስተውጭ የሚታይ አንዳች ሰሜት ላይኖር ይችላል። ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ ወደ ውስጥ ዘልቀህ ግባና፡ ቅርፊታችንን ልጠህ ማን መሆናችንን አሳየን፡ ጌታየ። ፍቀድ። ከዚያም በኋላ በመንፈስህ ሙላን፡ በእውነተኛ እና ንጹህ ልብ ሙላን። በዚህ የሰደት እና የከባድ ፈተናዎች ጊዜም፣ ቀኒቱን እየተጠባበቅን መንገድ ላይ ሰንጓዝ አብዝተህ፣ ጣፋጭ እና ተወዳጅ ትሆንልናለህ። እኛም ሰለ ከተማይቱ ሐጢያት፡ እንባ በጉንጫችን ሲፈስ፣ መንፈስ ቅዱስ ወደ ታች ተመልከቶ፦ "ይሄው ምልክት የማድርግበት አገኘሁ፡ እሱ የኔ ነው፣ እሷም የኔ ናት ይበለን።" ጌታ ሆይ፡ ይሁንልን። ዛሬ ከእኛ ዘንድ የተገኘ ይሁን። በኢየሱስ ሰም ጸለይን። አሜን።

በቀኑ መጨረሻ ወደ ወንዙ ሰመጣ፣
የመጨረሻው የሀዘን ንፋስ ሲነፍስ፤
መንገዱን የሚያሳይ ሚጠብቀኝ አለ፣
ዮርዳኖስን ብቻዬን አልሻገርም።

ዮርዳኖስን ብቻዬን አልሻገርም፡
ሰለ ሐጥያቴ ሰርየት ኢየሱስ ሞተልኝ፣
ጨለማውን ሳየው፡ እርሱ ይጠብቀኛል፣
ዮርዳኖስን ብቻዬን አልሻገርም።

177 አሁን እሱን ማወቅ እፈልጋለሁ። እጄን ያዝ፡ ምራኝ፣ ውድ ጌታየ፡ አጽናኝ። ጌታ ሆይ፡ ሰህተት በተባለው ነገር ሁሉ፡ ሰህተት በሚመስል ነገር ሁሉ ፊት፡ እዚህ ጸንቼ ልቁም። ማንም ምንም ቢል ግድ የለኝም፣ ጌታ ሆይ፣ ጸንቼ ልቁም። የምችለውን ሁሉ ሳደርግ፣ እንድቆም እርዳኝ። ጌታ ሆይ፡ እጄን

ይዘህ ወደ ሁሉ ምራኝ። እንድጸና፡ አንዳች ነገር አድርግ። ነገሮች በሚነሱ ጊዜ፣ የዚህም ዓለም ሀብቶች ክብር እና ዝና ሁሉ በመጡ ጊዜ፤ የሞተልኝን ብቻ ማየት እንድችል፡ አይኖቼን ዝጋ። ወዳጆቼን ሁሉ ቢያስከፍለኝም፣ ያለኝን ሁሉ ቢያስከፍለኝም፣ ምንም ማለት አይደለም፡ በመሰውያው ላይ ሁሉን አስማርካለሁ። ይኸው፡ በታማኝነት እጸናለሁ። አንድ ቀን ንፋሱ በፊቴ ሽው ሲል፣ ልቤም መወሰዱን እና ቀኖቼም ማለቃቸውን ሳውቅ፣ ጊዜየ ማብቃቱን እና ካርዶቼም ከማሰርያው መወሰዳቸውን ሳውቅ፡ ዮርዳኖስን ብቻዬን አልሻገርም። አብሮኝ ይሆናል። አዎን። ጨለማውን ሳየው፡ እርሱ ይጠብቀኛል፣ ዮርዳኖስን ብቻዬን አልሻገርም። እኔ አሁን ለእሱ ብቆም፡ ያኔ ለእኔ ይቆምልኛል። ስለ'ኔ ስለሞተው እኔ እኖራለሁ፡ ያኔ ህይወቴ ያማረ ይሆንልኛል። መጽናት የምፈልገው በዚህ ነው።

178 የታመሙ ሰዎች ያሉ ይመስለኛል። ካርዶችን አደለ? እረሳሁ'ኮ። ካርዶችን ሰጡ? የተሰጠ ካርድ አለ? የጸሎት ካርድ ያገኘ ሰው አለ? የለም።

179 መንፈስ ቅዱስን እየጠበቅኩት ነው። እምነት ካላችሁ፡ እመኑ ብቻ፡ አትጠራጠሩ። እግዚአብሔር ችግራችሁን ቢገልጥልኝ... ምንም ይሁን ምን፡ እኔ እንጃ፣ እጃችሁን ካወጣችሁ፡ እኔን የማታውቁ እኔም የማላውቃችሁ። ከዚያ እግዚአብሔር እዚህ ከገለጠው፣ ከጥፋት በፊት መልዕክቱን የሰጠ መልአክ እሱ እንደሆነ ታምናላችሁ ወይ፡ አሁንም ሌላኛው ጥፋት ከመሆኑ በፊት ይህን ያመጣው ያንኑ መልአክ መሆኑ ነው። ይሄን ታምናላችሁ? ካመናችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ። በጣም ጥሩ። በጣም ጥሩ ነው፣ እግዚአብሄር ይፈጽምልን።

180 እሱ አጠገቤ ቁጭ ያለው። ሌላም አጠገቤ የተቀመጠች፣ ወይዘሮ ሰናይደር እዚህ አለች፣ ወይም ወይዘሮ መርፊ እዚህ፣ ስሟ ማን ነው፣ እዚህ ቁጭ ያለችው። አውቃቸዋለሁ።

181 ይሄኛው ሰው አላውቀውም፣ ለእኔ እንግዳ ነው። እግዚአብሔር ግን ያውቀዋል። እግዚአብሔር አሁን ከገለጠ፡ ከኔ እንዳልሆነ ስንቶች ታውቃላችሁ...

182 እኔን አትዩኝ። ማይ፤ እኔ እስከሚገባኝ ድረስ የኬንታኪ ሂልቢሊ ነኝ። እኔ—በቂ ትምህርት እንኳን የለለኝ፡ ጭራሽ—የራሴን ስም ለመጻፍ፡ የምቸገር ነኝ። የማውቀው ግን አንድ አለ፡ እሱን አውቀዋለሁ። ማወቅ ምፈልገው እሱን ነው—ይህ ነው፡ እሱን ብቻ ነው። አሁን፣ አሁን ስለ'ኔ ሰዋሰው ምንም ትኩረት—አትስጡ።

183 እና ምናልባት ዛሬ ጠዋት ስብከቴ ሁሉም ከመስመር የወጣ እና ወዘተ ሊመስላችሁ ይችላል፤ አንዴ ከመጽሀፍ ቅዱስ ጋር አስተያዩት እና ዜሮ ታርጌት ላይ ትክክል ካልሆናችሁ እዩት። ከዚህ ጋር ካስተያያችሁት—ዒላማችሁ ውስጥ ካልገባላችሁ ተመልከቱ። እሱ ከተናገረው ነገር ጋር አያይዙት እንጂ፤ ከገዛ እሳቤዎቻችሁ ጋር አታስተያዩት። "ደጁ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው፤ ምክንያቱ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፣ መንገዱም ትልቅ ነውና፣ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፡" ሚልዮኖች ጊዜ ሚልዮኖች ይገቡበታል። ምናልባትም ውጤቱ አንድ ከሚልዮን ሳይሆን አይቀርም። ይኸው ነው። ያለው ይህ ነው። አሁን እሱ፡ ቁጥር አላስቀመጠም፡ ነገር ግን፦ "በኖህ ዘመን እንደነበረ፡ ሰምንት ነፍስ አለ።

በሶዶም ዘመን እንደነበረም፡ ሶስት።" ከዚህ ሁሉ ነገር፡ በእሳት የዳኑት፡ ሶስት ብቻ ነበሩ። አሁንም ያው ይሆናል!

184 አሁን፡ ሁላችሁ ትክክለኛ መንፈሳውያን ሰዎች ከሆናችሁ፤ እዚያ ጋር ቁጭ ያለውን ሰው እንድታዩት እፈልጋለሁ፡ ሳያቋርጥ ትኩር ብሎ ያየኛል። ራሱን ቀና አደአገ፡ እኔ አላውቀውም፤ አይቼው አላውቅም፣ ሰለሱ አንዳች ነገር አላውቅም። ብቻ እዚያ ጋር ቁጭ እንዳለ ነው። ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ጸሎት ላይ ነው፡ መነካካትን እያመቻቸ ነው። አሁን፡ ትክክል ነው። አሁን፡ እዚያ ጋር ከእኔ ርቆ የተቀመጠ ሰውየ፡ ይህ የመጀመርያ ቀን መገናኘታችን ነው... ጌታ ከተናገረኝ፡ እሱ በተቀመጠበት እንዳለ። እሱ ምን እንደሆነ—ምን እንደሆነ ከገለጠልኝ... እኔ—እሱን ማዳን አይቻለኝም። እኔ አልችልም፣ ይህ አይቻለኝም፡ ምክንያቱ እግዚአብሄር እራሱ ፈውሶታልና። የእናንተን እምነት ግን ከፍ ያደርጋል። ሁላችሁ እዩ አሁን፡ ያንን ያው መንፈስ አጠገቤ ቀርቧል። መጨረሻ ከመሆኑ በፊት፡ ኢየሱስ ይህ ይሆናል እንዳለ አስታውሱ። ይህ ሁሉም የመጨረሻው ምልክት ነው።

185 በቀደም ለት፡ እኔ እና ሌዮ ጎዳናው ላይ ቁጭ ብለን ነበርን፡ እና አንዳችን እያወራን ነበርን። በተደጋጋሚም ለውጥ እየመጣ ነው፣ ለውጥ እየመጣ ነው የሚል ስሜት ይሰማኝ ነበር። ስለሱ ሰናወራ፡ በአገልግሎቴ ላይ የሚሆን ለውጥ አይደለም፡ ከዚህ በላይ ሌላ ሰለሌለ፡ ለውጡ ግን በእኔ ላይ ነው። ሰዎች እንደፈለጉ፡ **ወዲህ** እና **ወዲያ** የሚመሩት እና የሚጎትቱት ዓይነት ተጎታች ሰው ነበርኩ። ጌታ ከረዥም ጊዜ በፊት አድርግ ያለኝ ነገር አድርጌ ብሆን ኖሮ፡ ዛሬ ያለሁበት ችግር ውስጥ ባልገባሁ ነበር። ቀጣይ ሳምንት ከጌታ ጋር ብቻየን ጊዜ ለማሳለፍ እወጣለሁ። አዎን፡ ጌታየ። ከሰማይ መሰማት—አለብኝ። ተጎታች መሆን አልፈልግም፡ በራሴ አቋም መጽናት እፈልጋለሁ።

186 ያ ሰውየ፡ በተደጋጋሚ ወደሱ አቅጣጫ ይመጣል፡ ሰውየው አምኖ፡ እዚያ ጀርባ ላይ ተቀምጧል፡ በርግጥም አምኗል። ጉባኤው ከጫፍ እስከጫፍ ስመለከተው፡ ሰው ሁሉ እሱን እያየ ነው። ሸክም አለበት፣ ልመና አለው፣ ሸክሙ ግን ስለ ሌላ ሰው ነው። አዎን። ሰለሌላ ሰው እየጸለይክ ነህ። በልብህ ውስጥ ሌላ ሰው ይዘሃል። ትክክል ነው፡ አይደለም'ዴ? ጓደኛህ ነው። ጓደኛህ ምን እንደገጠመው ብነግርህ፡ የእግዚአብሄር ባርያ መሆኔን ታምነኛለህ? የአልኮል ሱሰኛ ነው። አዎን። ትክክል ከሆነ፣ እጅህን ወደላይ አንሳ።

187 ታምናላችሁ? አንዳንዶች እጃቻቸውን አነሰተዋል፡ አንዲት ሴት እዚያ ጋር፣ ሌላም ሰው። አዎ። አዎን። አታውቂኝም አይደል? ለሁላችሁ እንግዳ ሰው ነኝ? እኔ አላውቃችሁም፡ ጌታ ግን ያውቃችኋል። ይሄን ታምናላችሁ? በልባችሁ ውስጥ ምን እንዳለ እግዚአብሄር ለእኔ ቢገልጽልኝ፡ ባርያው እንደሆንኩ ታምኑኛላችሁን? አንቺ ወጣት እመቤት፡ ያንቺ ችግር እዚያ ጋር ያለው ህጻን ልጅ ነው። አዎን። ልጁ ፊቱ ላይ ጭርት አለበት። ዶክተር ምንም ሊረዳው አልቻለም። ለአከባቢው እንግዳ ነሽ፡ አንቺ እና ቤተሰቦችሽ እዚያ ቁጭ ብላችኋል። ማን መሆንሽ ከየት እንደመጣሽ ጌታ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኚአለሽ? እምነሻል? እሱ ከወደደ የህጻኑን ፈውስ ለመቀበል ትፈልጊያለሽ? [ሴቲቱ፡ "አዎን" አለች።—አርታዒ] መልካም፡ ወደ መጣሽበት፡ ሶሚረሰት፡ ኬንታኪ መመለስ ትችያለሽ። እንደሚፈወሰም እመኚ፡ ካመንሽ ጭርቱ ህጻኑን ለቆ ይሄዳል።

188 ያቺን ቃል ስጠቅስ፡ አንድ ሰው በጉባኤው አዳራሽ ውስጥ ከሶሚረሰት፡ ኬንታኪ የሆነ ሰው ከኋላ ቆሞአል፣ የልብ ህመም አለበት፡ እየጸለየ ነው። እግዚአብሄር እንደሚፈውሳቸው ታምናላችሁ? በሙሉ ልባችሁ ካመናችሁ፡ እግዚአብሄር እንደሚፈውስ እና ጤነኛ እንደሚያደርጋችሁ እመኑ።

189 እዚያጋ፣ ከዚያች እመቤት፡ አጠገብ፡ እዚያጋ እጁ ያወጣ አንድ ሰው እንዳለ፡ እምናለሁ። አዎን፡ እጅሽን አይቻለሁ። እመቤት፡ እንግዳ ሰው ነኝ ላንቺ? አንቺን አላውቅሽም። ተገናኝተን አናውቅም። ባርያው እንደሆንኩ ታምኚናለሽ? [ሴቲቱ፡ “አዎን” አለች።—አርታዒ] አምነሻል? ልብሽ ውስጥ ሽክም ይሁን፡ የሆነ ነገር አለ። እግዚአብሄር ለእኔ ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምኚአለሽ፣ በክርስቶስ ውስጥ የነበረው ያው መንፈስ እንደሆነስ ታምኚአለሽ? አጠገብሽ ቁጭ ያለው ባልሽስ፡ እሱስ፡ ተመሳሳይ እምነት አለው? አንድ አይነት እምነት ታምናላችሁ? አጠገባችሁ ቁጭ ስላለች ህጻን ልጃችሁ በተመለከተ ነው። ትክክል፡ ካንሰር አለባት። እግዚአብሄር እንደሚፈውሳት ግን ታምናላችሁ? ካመናችሁ፡ እጃችሁን ከፍ አድርጉ። መልካም፡ እጆቻችሁን በህጻኗ ላይ አድርጉ።

190 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ በመንፈስህ ህልውና ፊት፡ ይህች ህጻን ልጅ የሚገድል ዲያብሎስ አወገዝኩት። በእምነት፡ በገዳዩ እና በህጻኗ መካከል የኢየሱስ ክርስቶስን ደም፡ አኖርኩ። በህይወት ትኑር። አሜን።

191 በእግዚአብሄር እመኑ። አትጠራጥሩ። “የማይቻል ነገር እንደሌለ፡ ካላመናችሁ።” ካመናችሁ፡ ሁሉም ይቻላል። በትክክል።

192 የሆነ ሰው፡ የሆነ ቦታ ላይ እጁ አውጥቷል፡ አንቺኛዋ፡ መጨረሻ ላይ ያለሽው እመቤት። የእግዚአብሄር ባርያ እንደሆንኩ ታምኛለሽ? አላውቅሽም፡ አታውቂኝም። እግዚአብሄር ችግሮችሽን ሊገልጥልኝ እንደሚችል ታምኚአለሽ? ኢየሱስን እንደ ፈዋስሽ ወይም እንደ አቅራቢሽ፡ ሁሉ ነገርሽ—ሁሉ ነገርሽ... ? ታምኚአለሽ ታዲያ? መልካም፡ የጭንቀት ችግር ነው ያለብሽ፡ የነበረብሽ ይህ ነው። ልክ ከሆነ፡ ህዝቡም እውነት እንደሆነ እንዲያዩ፡ ልክ ከሆነ፡ በእግርሽ ቁሚ። መልካም፡ አሁን ይለቅሻል። ቤትሽ ሂጂ እና ተፈወሺ። ጌታ ይባርክሽ።

ደግሞም፡ ከኬንታኪ ነሽ። አህ-ሀህ፡ ልክ ነው።

193 በአንቺ አጠገብ የተቀመጥችው እመቤት፡ እሷም ከኬንታኪ ናት። እሷም፡ ጭምር። አላውቅሽም፡ አውቅሻለሁ’ዴ? ነገር ግን ያለብሽኝ ችግር ልነግርሽ እችላለሁ። ችግርሽን ብነግርሽ፡ ክርስቶስን እንደ ፈዋሽሽ ትቀበዪዋለሽ? ዳሌሽ ውስጥ ነው። ትክክል ከሆነ፡ ሰዎች እንዲያዩ፡ እጅሽን በደንብ ከፍ አድርጊው። መልካም፡ አሁን ቤትሽ ሂጂ፡ ይለቅሻል። እምነትሽ አድኖሻል።

እንድታምኑ ሞግታችኋለሁ። በእምነታችሁ እንድታምኑ እጋብዛችኋለሁ።

194 እዚህ ጋር፡ እየጸለየች ያለችው እመቤት፡ መሀርቧን ፊቷ ላይ አድርጋለች። እኔ አንቺን አላውቅሽም። እግዚአብሄር ግን ያውቅሻል። ከጆልየት፤ ኤሊኖይ ነሽ፡ እጢ አለብሽ። ይህ ፍጹም እውነት ነው። ሊደንቅሽ ይችላል... (አዎ፡ እሷ ማለት—ሮሴላ ያመጣቻት ሴት ናት። አዎን። ቆይ፡ ይሄ እሷ ነግራኛለች፡ ነገር ግን ሴቱቱን በፍጹም እንደማላውቃት ፍጹም አታውቅም። እውነት ነው። ይህ ያደረገ የሴቲቱ እምነት ታላቅነት ነው።) አንድ ነገር ልንገርሽ—እኔ እንደማላውቅሽ ታውቂአለሽ። በወንበሮቹ መጨረሻ ላይ ተቀምጦ ስላለ፡

የታመመ ህጻን እየጸለይሽ ነሽ። ልጅሽ ነው። አዎን። አሜን። ይህ እኔ እንደማላውቅ ታውቂአለሽ።

195 ይሄው፡ መንፈስ ቅዱስ ነው! ታምኛለሽ? ተቀብለሻል? እንግዲያውስ ይህ ትክክል ከሆነ፡ "ደጁ ጠባብ ነው፡ መንገዱም ቀጭን ነው" ሰል ትክክል ነዋ። የእግዚአብሄር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አሁን እዚህ አለ። የህያው የእግዚአብሄር መንፈስ አሁን እዚህ አለ። ታምናላችሁ? ስለዚህ፡ ለማሳሰብ ያክል ማንንም ለመፈወስ አልችልም ተራ ሰው ነኝ፡ ፈዋሽ አይደለሁም፡ ነገር ግን የእግዚአብሄር መንፈስ እራሱን ለመግለጥ እኔን መረጠ። ምንም ትምህርት የለኝም። ምንም አይነት እውቀትም የለኝም። ይህን የሚያደርገው ግን የእራሱ መንፈስ ነው፡ እያችሁ፡ የነገርኳችሁ ነገር እውነት እንደሆነ እንድታውቁም ፈልጓል።

196 እውነቱ ይሄው ነው፡ ካመናችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ አሁን ሁላችሁም ጤነኛ ያደርጋችኋል። አሁን ልክ እንደ... በኪንግሰተን፡ በዚያ የነበሩት እና ሚሽነሪዎች እንዳዩት ሁሉ፡ በኪንግስተን መስራቱን፣ በሺዎች እንደተፈወሱ ሁሉ፣ አሁን እዚህ አሜሪካ ላይ እንደያዝነው መንገድ ለምን አይሰራም? ማመን ለምን ተሳነን? ምክንያቱማ ትንሿ ሽጉጥ ኢላማዋን ማሻገር ሰላልቻልን ነው። አምናችኋል? እጆቻችሁን ከፍ አድርጉ።

197 አሁን፡ እነኚህ እጆች፡ በአጠገባችሁ ባለው ሰው ላይ አኑሯቸው፣ እኔም እዚህ ሆኜ እጸልያለሁ፡ ከእንግዲህ ወዲህ በልባችሁ ምንም አይነት ጥርጣሬ አይኑራችሁ፡ በዚህ ያበቃለታል።

198 ኦህ፡ ማይ፡ ወንድም ነቪል! አቤት ምኞቴ፣ አቤት ጸሎቴ፣ አቤት... በራሴ ችየ የቆምኩ ሊመስላችሁ ይችላል፤ አይደለሁም። የት እንዳለሁ በትክክል አውቃለሁ። እኔ ይህን ትንሽ ነገር ወደ እናንተ ብቻ ማስገባት በቻልኩ! በዚህ ጠዋት የአምላክ ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በዚህ ህዝብ መህል መሆኑን አስተውላችኋል፤ አሁን፡ እራሱን እያሳየ፡ አሁን ህያው እንደሆነ?

እኮ፡ አንተ'ኮ ብለሃል፡ "ይህን ያልከው፡ ወንድም ብራንሃም **አንተ** ነህ።"

199 ይህን ማለት እንዴት ይቻለኛል? እኔ አንቺን አላውቅሽም። ሌላም በቲቢ የተያዘች ሴት አለች። እህት፡ ተፈውሰሻል። ተባረኪ። ይቅርታ አርጊልኝ፡ በቲቢ ለታመመች ሴት እየጸለይሽ ነበር፡ ምክንያቱ ጸጉረ-ሽበታም ሴት። አዎን። መልካም፡ እመኑት። በጣም ጥሩ። እሱ እዚህ ነው። የእሱ መገኘት ነው።

200 አሁን እሱ እንዲህ ብሏል፦ "ያመኑት እነዚህ ምልክት ይከተሉአቸዋል። እጆቻቸው በበሽተኞች ላይ ቢጭኑ፡ ይፈወሳሉ።" እሱ እንዴት ሊዋሽ ይችላል? እያችሁ፡ የሱ ጉዳይ አይደለም፣ የእኔም ጉዳይ አይደለም፣ በራሳችሁ ላይ ነው። አሁን እመኑ።

201 አሁን እዚያ ማዶ ላይ የተቀመጠችውን ሴት ትታየኛለች፡ እጅግ ብዙ እምነት አላት። እሷ እና ባለቤቷ በቅርብ ነው ወደ ጌታ የመጡት። በጉባኤው ውስጥ ናት፡ የመዛነፍ ችግር ገጥሟት ዶክተርም ቀዶ ጥገና ሊያደርግላት ነበር፡ ልጁ ግን ለመወለድ ዝግጁ ሆኖ ነበር። አሁንም ዶክተሩ ከዚያ በኋላ ቀዶ ጥገና ሊያደርግላት ፈለገ፡ ልጁ ግን ተወለደ ከዚያ በኋላ ምንም አይነት የሰውነት መዛነፍ አላገኙም። ሁሉም ጠፋ። እያችሁ? ለምን? እንደው ተዘጋጀችበት... አንድም ቀን ወደዚህ መድረክ መጥታ አታውቅም። ባለችበት

ተዘጋጅታ ታምናለች። እንደሱ ነው አይደል፡ እንደሆነ አምናለሁ፡ ከኋላ፡ ወይዘሮ ግሪን? ትክክል። እጇን አያችሁ? ጠቅልሎ ሰለጠፋ፡ ዶክተሩ ምንም አይነት መዛነፍ ማግኘት አልቻለም። ለምን? ሰላመነች፡ ደፍራ ወጥታ፡ "እውነት ነው ሰላለች!"

202 አሁንም እናንተ ተመሳሳይ ነገር አድርጉ፡ በውስጣችሁ ያለው ጉዳት ሁሉ ይለቃቿል። አምላክ ሆይ፡ ማን—እሰኪ ወደ ሰው አካል አንድን ነገር ማሰረጽ ማን ይችላል፣ ያንን መርዞ ሊገድለው፡ በሰውየው እግር ላይ የነደፈው፡ የእባቡን መርዝ፤ ውድያው ማሰቆም ችሎ ያመከነው፡ በሰውነታችሁ ውሰጥ ላለው ህመም ምንኛ መግደል ይቻለው። ምክንያቱ፡ ሰውየው ተሰፋ ቆርጦ ነበር፡ እርዳታ ማግኘት ነበረበት። እናንተም ማግኘት አለባችሁ። ከሌላችሁ፡ ትሞታላችሁ።

203 አሁን እጆቻችሁ በሌላ ሰው ላይ አኑሯቸው። ለራሳችሁ አትጸልዩ፣ ከጎናችሁ ላለው ሰው ጸልዩ። ክርሰቲያን-ማለት እንዲህ ነው።

204 እወቁት፣ ይህን ተማሩ፣ ለሌሎች የምታደርጉት ሁሉ፣ ለክርሰቶሰ አደረጋችሁ። ለሌላ ሰው መልካም ሰትሆን ለክርሰቶሰ መልካም እየሆንክ ነው። ሌላ ሰውን ብትበድሉ፡ ክርሰቶሰን ትበድላላችሁ። ኦህ፡ ማይ!

205 እንደው፡ ብቻ ይህ ነገር ማሻገር በቻልኩ ኖሮ፡ ሰዎች ማየት እንዲችሉ ባረግኩ ኖሮ፡ እኔ የማየውን ሁሉ እና የሚሰማኝን ሁሉ፡ አሁን እየተከናወነ እንዳለ የማውቀው ሁሉ፡ አያችሁ። ክርሰቶሰ የዛሬው ጠዋት መልዕክት ምን ያህል እየገፋው እንዳለ፣ ይህም በቀጥታ በሰዎች ልብ ውሰጥ ገብቶ ግርምትን ለማድረግ ሳይሆን፡ አንዳች ነገር እንዲፈጥር ነው፡ ሰሜት ሳይሆን (አብሮ የሚመጣ ነው)፣ ነገር ግን ለጠላት አንዲት ኢንች የማይሰጥ፣ የማይወድቅ እምነት ለመገንባት ነው።

206 አሁን፡ ጸሎቴን ይሰማኛል፣ የእናንተም ይሰማል። እኔ ለሁላችሁ ሰጸልይ፡ እናንተም አንዱ ለሌላው ጸልዩ።

207 ጌታ ሆይ፡ ይህ ታላቅ ወሳኝ ጊዜ፣ ይህ ለብዙዎች፡ በሞት እና በህይወት መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚያመለክት እንገነዘባለን። እኔም ጌታ ሆይ፣ በፍጹም ልቤ መጸለይ እንዳለብኝ አውቃለሁና፣ በአንተ ፊት እንቀጠቀጣለሁ። ምንም እንኳን በሌላ በአምሰት ደቂቃዎች ውሰጥ በመካከላችን የታመመ ሰው ላይኖር ቢችልም፣ እዚህ ያለ እያንዳንዱ ሰው ግን እዚህ መሆንህን ይገነዘባል። ይሄው ዛሬ ጠዋት ቆመዋል፣ ጌታ ሆይ። እኔ ሰለ እነሱ አንዳች ነገር እንደማላውቅ፣ የሚያውቁ ሰዎች፤ እጆቻቸውን ወደ ላይ ያነሱ። መንፈሰህ ግን ያውቃቸዋል። አንተ የልባቸውን ምሰጢር ታውቃለህ፣ ሰቃያቸውን እና መከራቸውሰ ምንኛ ታውቃለህ! ከዚያ፡ ጌታ ሆይ፡ መንፈሰህ የታመሙትን አካሎቻቸውን የሚነካው ዛሬ ይሁን፡ አረ እንደው አሁን ይሁን። ሰጠን፡ ጌታ ሆይ። አንዱ ለሌላው ይጸልያሉ።

208 እኔም እጸልያለሁ፣ ውድ አምላክ ሆይ፣ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳይጠራጠሩት፤ መንፈሰ ቅዱሰ እውነት ያድርግላቸው። እናም ጌታ ሆይ፡ ከዚህ የሰጋ በሽታ ይልቅ የከፋ፡ ሌላ በሽታ አለ፣ መንፈሳዊ በሽታ ነው። እያንዳንዱ ልብ ይከፈት።

209 ጌታ ሆይ፣ እንዴት ቢሆን ነው ያኔ ከአብርሃም ጎን የቆምኸው፣ ቃል ሲናገር፡ “ከበስተጀርባህ” የነበረችውን ሳራን የነገርክበትን፡ ይህ አንድ አይነት ነገር የፈጸምከው፣ “በድንኳኑ ውስጥ ሳቀች፡” አንተም ነገርካት። አብራሃምም ታላቁ አምላክ ኤሎሂም፡ መሆንህን አወቀ። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ከዓይኑ ተሰወርክበት።

210 ጌታ ሆይ፣ ኢየሱስም ቆሞ ያንኑ ሲያደርግ፣ “አብርሃምን ‘አባታችን’ ብላችሁ ትጠሩታላችሁ፡ በተጨማሪም ቅዱሳት መጻሕት እናውቃለን ትላላችሁ፡” አልካቸው። “ቅዱሳት መጻሕፍትን እና የእግዚአብሔርን ኃይል ስለማታውቁ ትስታላችሁ፡” አልካቸው። እነሱ ግን “ቡኤልዘቡል” አሉት።

211 በመጨረሻዎቹ ቀናት ግን መንፈስህን እንደገና እንደምታፈሰው ቃል ገብተሃል። ነቢዩም “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል፡” ብሏልና። እኛም ይሄው አለን።

212 ስካራም ማታ ወደ ቤቱ ለመሄድ እንደሚንገዳገድ፣ ይህ ሕገወጥ ዓለምም በኃጢአት ስር ሰትንከባለል፣ የእሳተ ጎመራ ብናኝ፡ እስከማይገኝባት ድረስ፡ በቅርብ ጊዜ፡ ከወግቧ ትፈነዳዳለች። ጊዜውም እየቆጠረ እንደሆነ እናያለን።

213 እግዚአብሔር ሆይ ፣ ጥርጣሬን ሁሉ ከእኛ አርቅ። አሁኑኑ ወደ ዑደት አዙረን። መንፈስ ቅዱስ ሆይ፡ ና። አሁን በዚህ በታናሹ መንጋ ላይ፡ ታላላቅ ክንፎችህን ዘርጋባቸው፣ በልባቸው ውስጥም እራስህን አስርጽና፣ በመለኮታዊ መገኘት ውስጥ እንዳለህ ይወቁ፣ “ደዌሽን ሁሉ የምፈውሰ ጌታ እኔ ነኝ፡” አንተ መሆንህን። መገኘትህም ዛሬ ጠዋት ከዚህ እንዲሄዱ የሚያደርጋቸው ምክንያት፡ በልባቸው ላይ የሆነ ነገር ያድርግ፣ ባላቸው አቅም ሁሉ በማመን። የታመመ እና የተመታ ሰው ሁሉ ይፈወስ።

214 እኔም፡ እንደ አገልጋይህ፡ ቆሜ ዲያብሎስን ሁሉ ገሰጽኩ፣ በሽታን ሁሉ ገሰጻለሁ፣ ሰይጣንን ገሰጽኩት።

215 አንተ ወድቀሃል፡ አስመሳይ ነህ ሌላ አይደለም። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እጅህን በዚህ ላይ እንጠራታለን። እና እንደ ባርያው፣ ከእግዚአብሄር ቃል ጋር እንዲታረቁ እና እንዲቃኑ ቃሉን ሰብኬ ለህዝቡ እውነትን ተናግሬአለሁ፣ አንተ ሰይጣን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ገሰጽኩህ። ለመፈወስ ከሩቅ እና ከቅርብ ከመጡት ከእነዚህ ሰዎች፡ ከእያንዳንድሰቸው ራቅ። ከጉባኤው እና ከዚህ ህዝብ ውጣ። በሕያው በእግዚአብሔር አዝሃለሁ። መጽሐፍ ቅዱስም፡- “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች” ብሏል። እናም ዛሬ ጠዋት፡ ብዙ ጻድቃን እጃቸውን በታመሙ ሰዎች ላይ ጭነዋል። ኦህ፣ ሰይጣን፣ ክብሩን ከእነሱ ለመውሰድ፡ እኔ እንደሆንኩ እንዲያሰቡ ትፈልጋለህ። ግን በእግዚአብሔር ላይ ያላቸው እምነትም፡ እንዲሁ፣ እግዚአብሔርን ያምናሉና! ከእምነታቸው የተነሳ፡ ትርቃለህ። ስለዚህ ጓዝህን ከዚህ አርቅና እና ወደ መኖርያህ ወደ ውጭ ጨለማ ሂድ። በእግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን፣ እና በመልአኩ በተሰጠኝ ተልዕኮ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ገሰጽኩህ። አሁን፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፣ ሂድ ነጻ ይሁኑ። አሜን።

216 መፈወሳችሁን፡ በሙሉ ልባችሁ፡ አምናችኋል? እጆቻችሁ እያነሳችሁ፡ እንዲህ በሉ፦ “አሁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ፈዋሼ እቀበላለሁ። ጥላዎች ሁሉ ከእኔ ጠፍተዋል። አሁን በኃይሉ ሙላት፣ የመገኘቱ በረከት እቀበላዋለሁ። እርሱን ተቀበልኩት።”

እምነቴ አንተን ይናፍቃል፣
አንተ የቀራንዮ በግ፣
አዳኝ መለኮታዊ፡
አሁን ሰጸልይ ሰማኝ፣
ኃጢአቴን አሰወግድልኝ፣
እንድሰት አትፍቀድ
ከጎንህ አልራቅ።

አሁን እጆቻችንን ደሰ በሚል ሁኔታ ወደ እሱ ከፍ እናድርግ።

በህይወት ድንግዝግዝ ሰጓዝ፡
ሀዘን በዙርያዬ ሲዘረጋ፣
(አምላክ ሆይ!) አንተው መሪ ሁነኝ፡
ጨለማን ገፈህ ብርሃን አርግልኝ፡
ሀዘንን ጠርገህ፡ ፍርሃትን ገፈህ፡
እንድሰት አትፍቀድ
ከጎንህ አልራቅ።

... ሀብታም ጸጋ!

**ደጁ ጠባብ ነው** AMH59-0301M

(Strait Is The Gate)

**የቤተክርሰትያኒቱ መተካካት**

ይህ መልዕክት በወንድም ዊልያም ማርዮን ብራንሃም በኢንግሊዘኛ በ የተላለፈ መልዕክት መጋቢት 1፡ 1959፡ እሁድ ጠዋት፡ ጀፈርሰንቪል፣ ኢንዲያና በሚገኝ በብራንሃም ተበርናክል፤ ዩ.ኤሰ.ኤ፣ ከማግኔቲክ ቴፕ ቅጂ ተወሰዶ ሳይሸራረፍ ወደ ኢንግሊዘኛ ተጽፏል። ይህ የአማርኛው እትም በቮይሰ ኦቭ ጋድ ሪከርዲንግሰ ተተርጉሞ ተሰራጭቷል።

AMHARIC

©2022 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው።

ተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ከፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org